# ሐመር

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት፣
ሥርዓተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት
ጠብቆ የሚወጣ

ሐምሌ/ ፳፻፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በኅትመትና
ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ዋና ክፍል
በመጽሔት ዝግጅት ክፍል የሚዘጋጅ
ትምህርታዊ መጽሔት



## ማውጫ


የማኅበሩ መልእክት
"ክፉውን ከእናንተ አርቁ" ፪

ዐውደ ስብከት
ከንቱ ውዳሴ ፭

ትምህርተ ሃይማኖት
በቃልህ አዝዝ ልጄም ይድናል ፲

ዐቢይ ጉዳይ
ጊዜው ለጽድቅ የምንበቃበትን የምንሠራበት እንጂ ወደ ጥፋት የምንነዳበት አይሁን ፲፭

ዐቢይ ጉዳይ
ክብረ ክህነት ፳፩

ክርስትና በማኅበራዊ ሕይወት
"መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ" ፳፯

ኪነ ጥበብ
ባለህበት ጽና ፴፩

አቦጊዳ የግእዝ ትምህርት
ቅጽል ፴፯


"ማኅበረ ቅዱሳን" እግዚአብሔር ያከበራቸው
የነቢያት፣ የሐዋርያት፣ የጻድቃን፣ የሰማዕታት
በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ ትሩፋትና
አማላጅነት የሚዘከርበት በመሆኑ ይኽን ስያሜ
አግኝቷል።


## የዝግጅት ክፍሉ

ስልክ ፲፩-፳-፩፪-፪፳-፬፱
ፖ.ሣ.ቁ ፳፲፲፯፳
ኢ-ሜይል magazine@eotcmk.org
የማኅበረ ቅዱሳን ሕዝብ ግንኙነት ስልክ
፲፩-፩-፭፭-፫፪-፫፱
የልማት ተቋም የስርጭት ክፍል ስልክ
፲፩-፩-፪፫፬፭-፪፱
የማስታወቂያ ዝግጅት ክፍል ስልክ
፲፱፬፪-፫፳-፩፯-፱፩

ም/ዋና አዘጋጆች
ዲያቆን ያረጋል አበጋዝ
አድራሻ፡- ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ
ወረዳ ፲፭ የቤት ቁ. ፺፪፲

ከፍተኛ ሪፖርተር
ዲ/ን ዐቢይ ሙሉቀን

ሌይ አውት ዲዛይነር
ግደይ ገብሬ

ጸሓፊ
ገነት ታደሰ

# “ክፉውን ከእናንተ አርቁ” (፩ኛ ቆሮ. ፭፥፲፫)

## የማህበሩ መልእክት

ኢትዮጵያ ጥንታዊት ሐዋርያዊት ርትዕት የሆነችው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ሀገር ናት። ኢትዮጵያ ሀገረ እግዚአብሔር መባልዋም እግዚአብሔርን በብሉይ ኪዳን የአመለከች፣ በልደቱ ቤተ ልሔም ድረስ አምኃ ይዛ የሄደችና ሰግዳ መባዕ ያቀረበች (መዝ. ፸፩፥፱-፲፩)፣ በስደቱ ጌታን ከእናቱ ጋር የተቀበለች፣ በጃንደረባው አማካይነት በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ወንጌልን ተሰብካና አምና በሐዋርያት እጅ ተጠምቃ ክርስትናን የተቀበለች (ሐዋ.፰፥፳፮-፵) ሀገር በመሆኗ ነው። ወደ ፈጣሪዋ የተዘረጉት እጆቿ በዘመነ ብሉይም ሆነ በዘመነ ሐዲስ ከማንም አገር በተለየ ሁኔታ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ከእግዚአብሔር ተቀብለዋል። ለአብነትም በዘመነ ብሉይ ታቦተ ጽዮን ከብዙ ንዋያተ ቅድሳት ጋር፣ በዘመነ ሐዲስ ኪዳን ደግሞ ግማደ መስቀሉንና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል። ይህ ሁሉ የሆነው አባቶቻችን በሃይማኖታቸው ጸንተው በጎ ምግባር ሠርተው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መኖር በመቻላቸው ነው።

በዚህም አባቶቻችን ሃይማኖታቸውን ከአገራቸው አልፈው በኢየሩሳሌምና በሌላውም ዓለም አስፋፍተዋል። የእግዚአብሔር ቅዱሳንም ኢትዮጵያን በመንፈስ ተረድተው ከሀገራቸው ተሰደው ተሸሽገውባታል፤ ሃይማኖትንም ሰብከውባታል። ለአብነትም ዘጠኙ ቅዱሳንንና አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስን መጥቀስ ይቻላል። በዚህም ቤተ ክርስቲያን አገሪቱን በታሪክ በቅርስና በጀግንነት ማማ ላይ ሆና ከፍ ብላ እንድትታይ አብቅታለች። የክርስትና ሃይማኖት በሌሎች አገሮች የተሰበከው በብዙ የደም ሰማዕትነት ነው። በሀገራችን ኢትዮጵያ ግን በእግዚአብሔር ቸርነትና ፈቃድ ሃይማኖት ከቤተ መንግሥቱ ጀምሮ ወደ ሕዝቡ ስለተሰበከ የክርስትናው ሃይማኖት በሰላም እንዲሰበክ ጥሩ ዕድል ፈጥሯል።

ይሁንና ይህን የሰላምና የጥበብ ጉዞ ለማደናቀፍ ጠላት ተኝቶ አያውቅም። ከምንጩ ቀድታ በሰላም ስትመራው የኖረችውን ክርስትና ከምንጩ ያልቀዱት በተንሸዋረረ መንገድ የተሰበኩት ምዕራባውያኑ ግን መስመሯን ሊያስቱ ሲታገሏት ሲፈታተኗት መኖራቸው የማይዘነጋ ሐቅ ነው። ጥቂቶቹን ብናይ በአፄ ሱሱንዮስ ዘመን፣ በፋሽሽት ጣሊያን ወረራና በየጊዜው ነገሥታቱን በመሣሪያና በመሳሉት በመደለል ቤተ ክርስቲያንን ለመከፋፈል የተከናወኑ ተግባራት ተጠቃሽ ናቸው። ይሁን እንጂ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ጴጥሮስን አንተ ዐለት ነህ ባንተ ዐለትነት ቤተ ክርስቲያንን እሠራታለሁ። የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም። (ማቴ.፲፮፥፲፰) እንዳለው አጽራረ ቤተ ክርስቲያናት ምንም ቢጥሩ ቤተ ክርስቲያንን ሊያጠፉ አልቻሉም። እነርሱ እየጠፉ ቤተ ክርስቲያን ግን እያበበች፣ እያፈራችና እየተስፋፋች ኖረች እንጂ።

ዲያብሎስ በየዘመናቱ በቤተ ክርስቲያን ላይ በውስጥም በውጭም ፈተና እያስነሣና የፈተናውን መልክ እየለዋወጠ ምእመናንን ሲያምስና ሲያውክ ኖሯል። በውጭ ካሉት የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች በሚነሣ ፈተና ብቻ ሳይሆን በውስጥ ባሉ ሐሰተኛ መምህራንም ፈተናው እንደሚነሣ መረዳት ያስፈልጋል። በእኛ ዘመን ያለው ዋና ፈተና ደግሞ የዘረኝነትና የፖለቲካ መንፈስ ነው። ድንበር የለሽ የሆነውን ዋናውን የክርስትና ዓላማና ጉዞ ዘንግተን በዘር በጎሣ በቋንቋ በአካባቢ እየተከፋፈልን በመሆኑ ይህ ክፉ ሥራችን ቤተክስቲያንን ማዕበል ሆኖ እያናወጣት ይገኛል። ቤተክርስቲያን ሰማያዊት ናት። ቤተክርስቲያን አምነው የተጠመቁ ከእርስዋ ለተወለዱ ሁሉ እናት ናት። ዘር ቀለም ቋንቋ እውቀት ውበት ጉስቁልና ወንዝ መንደር አይወስናትም። ድንበር የለሽም ናትና በእኛ የአስተሳሰብ ልክ ልንወስናት አንችልም።

አባቶቻችን በእምነት ጉዞ ውስጥ አንዳንድ የአመለካከት መለያየቶች እንኳ ሲፈጠሩ ተረጋግተው ተወያይተው ተከራክረው ለመፍታትና ፍቅርና አንድነት ለመፍጠር ብዙ

ጥረት ያደርጉ የነበረው ፍቅርን ማስቀደም ስለሚበልጥ ነው፡፡ ወደ መጨረሻው ውሳኔ የሚደርሱት አማራጭ ከጠፋና የሃይማት ልዩነት ሆኖ ሲገኝ ነው ። ያውም ቢሆን እንደዘመናችን ለግል ፍላጎትና ጥቅም ወይም የሥልጣን ፍላጎት ሳይሆን ቤተ ክርስቲያንንና መንጋውን ከአደጋ ለመታደግ ሲሉ ነበር የተፈለገውን መሥዋዕትነት ለመክፈል የሚተጉት፡፡ በዘመናችን ሕግና ሥርዓት በሰፈነበት ተወያይቶና ተመካክሮ ጉዳዮችን በሰላማዊ መንገድ መፍታት ሲቻል በሠለጠነ ዘመን የቤተ ክርስቲያንን አንድነት የአገርን ሰላማዊ ጉዞ የምእመናንን ፍቅርና አንድነት በሚያናጋ መልኩ ፅንፍ ይዞ ያለመንገዱ መሄድ ለማንም የማይጠቅም ነው፡፡

**ቀደምት አባቶቻችን ሃይማኖቱን ብቻ ሳይሆን በእምነት ጉዞ ውስጥ የምንመራበትን ሕግና ሥርዓት ትልቅ መንፈሳዊና ተቋማዊ የመንፈስ ቅዱስ አሠራር ቅዱስ ሲኖዶስን መሥርተው አልፈዋል፡፡**

ይህን የሚያሰኘን በምሥራቅ ጎጃም ከቅባት ትምህርት ጋር በተያያዘ የተከሠተው የመለያየት አጀንዳ ነው፡፡ በመጀመሪያ በጥንቃቄ ማየት ያለብን መለያየት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ አለመሆኑን ነው፡፡ ከወገኖቻችን እንደችግር የተነሡትም ጉዳዮች መፍትሔ የሚፈልጉ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ቢሆኑም ለቀኖና እና በሕግ ጥሰት የሚዳርጉ ግን ሊሆኑ አይገባም፡፡ በአንዲት ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ዶግማና ቀኖና የሚመራ ማንኛውም ተከታይ የሐዋርያትን ዶግማና ቀኖና በግብታዊነት ሊንድ ሊሽር ፈጽሞ አይችልም፡፡ ማዕከላዊነትን ሳይጠብቁ በየፊናቸው የፈለጋቸውን የመሾም በፈለጉት መንገድ የመጓዝ አካሄድ የፕሮቴስታንቶች ባህል እንጂ የኦርቶዶክሳውያን ትውፊትም ባህልም አይደለም፡፡ ኦርዶቶዶክስ ተዋሕዶ ማእከላዊነትን የጠበቀ አሠራር ነው የምትከተለው፡፡ የምትመራውም ከፍ ባለ ሐዋርያዊ ልዕልና በቅዱስ ሲኖዶስ ነው፡፡ ከቤተ ክርስቲያን እውቅና፣ ሕግና ቀኖና ውጭ ሊቀ ጳጳስ እስከ መሾም መድረስ አሳዛኝና አስደንጋጭ ኦርቶዶክሳዊ ያይደለ ምናልባትም ሁሉም ሰው ያልተገነዘበው ተቆርቋሪ መስሎ ቀርቦ የዋሁን ሕዝብ በማነሳሳት በኩል የጠላት እጅ ሊኖርበት የሚችል ባእድ ተግባር ነው፡፡

ቀደምት አባቶቻችን ሃይማኖቱን ብቻ ሳይሆን በእምነት ጉዞ ውስጥ የምንመራበትን ሕግና ሥርዓት ትልቅ መንፈሳዊና ተቋማዊ የመንፈስ ቅዱስ አሠራር ቅዱስ ሲኖዶስን መሥርተው አልፈዋል፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊት በመሆኗ የትምህርት የቀኖና ሥርዓት አላት፡፡ ለመሾምም ለመሻርም ለማጥመቅም ለማውገዝም የራስዋ ሐዋርያዊ ቀኖና አላት፡፡ በቤተ ክርስቲያኒቱ ሥር ያሉ ተቋማትም የሚመሩት በቅዱስ ሲኖዶሱ ውሳኔ ነው፡፡ ከቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ የወጣ ነገር በሚኖርበት ጊዜ ጉዳዩን ለቅዱስ ሲኖዶስ አቅርቦ ሐዋርያዊ የሆነውን ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ተከትሎ የሚስተካከል ጉዳይ እንጂ እከሌ ወእከሊት እንዲህ አለ እንዲያ አለ ተብሎ በወፍ በረር ወሬ ቤተ ክርስቲያንን የሚያክል ታላቅ ነገር የሚለያይ ሥራ መሥራት በምንም ሚዛን ትክክል ሊሆን አይችልም፡፡ ቆም ብሎ ማሰብ ማረምም ይገባል፡፡

የቤተ ክርስቲያንን ወገኖች አይጠቅምም፡፡ ከጀርባ ሆነው የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ለማናጋት ለሚሠሩ አፅራረ ቤተ ክርስቲያን ለጥፋት ተልኮአቸው እድል መስጠት ነው፡፡

በአንዲት ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባላት መካከል የቀኖና ወይም የዶግማ አረዳድና አተገባበር ላይ ልዩነት ከተፈጠረ በትምህርት የሚመለሰውን በትምህርት ፣ በውይይት የሚታረመውን በውይይት፣ በቀኖና ውሳኔ የሚፈታውን በውሳኔ ማስተካካል ተገቢ ነው:: ከዚህ የወጣና የማይታረም ካለ አውግዞ እስከ  መለየት ሊዘልቅ ይችላል:: የቤተ ክርስያንን ሐዋርያዊ ዶግማና ቀኖና የማስጠበቅ ኃላፊነት ደግሞ የቅዱስ ሲኖዶስ ነው:: በዚህ ጉዳይ ላይ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ልዩ ትኩረትና ጥንቃቄ የተመላው በጥበብና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የታገዘ አካሄድና ውሳኔ ሊሰጡበት ይገባል::

**አፅራረ ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜም ቤተ ክርስቲያንን ለማዳከም ምእመናንን ለመከፋል በየዘመናቱ የሚፈጥሯቸውን ተንኮሎች አባቶቻችን በጥንቃቄ ይዘው በምክርና በትምህርት እያከሙ ያቆዩትን ጉዳይ ምክንያት ፈልጎ በመቀስቀስ ከቤተ ክርስቲያን የመገንጠል፣ ሕዝብን የመከፋፈልና ለቤተ ክርስቲያን ጠላቶች መሣሪያ የመሆን አዝማሚያ ሊታረም ይገባል።**

አፅራረ ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜም ቤተ ክርስቲያንን ለማዳከም ምእመናንን ለመከፋል በየዘመናቱ የሚፈጥሯቸውን ተንኮሎች አባቶቻችን በጥንቃቄ ይዘው በምክርና በትምህርት እያከሙ ያቆዩትን ጉዳይ ምክንያት ፈልጎ በመቀስቀስ ከቤተ ክርስቲያን የመገንጠል፣ ሕዝብን የመከፋፈልና ለቤተ ክርስቲያን ጠላቶች መሣሪያ የመሆን አዝማሚያ ሊታረም ይገባል::  ይህን የቤተ ክርስቲያንን ልዕልና ለማኮሰስ፣ ሰላሟን ለማደፍረስ ለሚሠሩ አካላት መሣሪያ መሆን ነው:: ይህን ዝም ብለን የምንመለከተው ጉዳይ አይደለም:: ቅዱስ ሲኖዶሱ በጉዳዩ ተወያይቶ አስተማሪ የሆነ በቤተ ክርስቲያን ዶግማና ቀኖና ላይ የተመሠረተ የእርምት ርምጃ ሊወስድበት በቦታውም ሄዶ ሕዝቡን ማወያየት ማስተማር ግልጽ ያልሆኑ ጉዳዮችን በትምህርት በሥልጠናና በውይይት መፍታት ያስፈልጋል::

ቀኖናዊ ውሳኔዎች የሚያስፈልጉአቸውን ጉዳዮችን ደግሞ ለይቶ  መወሰን ይገባል:: እንደዚህ በማድረግ ክፉ ልብና ሕሊናን በትምህርትና በንስሓ በተግሣጽም ጭምር ማስተካከል ካልተቻለ እሾሁ ካደገ መንቀል ይቸግራል:: ጠላት በከፈተው በር ለመግባት ደግሞ ብዙ አሰፍስፎ የሚጠብቅ ወንበዴ ስላለ በዛ ቀዳዳና ክፍተት ገብቶ መንጋውን ይዘርፋል:: ክፉውን ሕሊና አስወግደን  በጎ በሆነ ሕሊና ጠንክሮና ተግቶ አብሮ መሥራትን ይጠይቃል:: ይህን ክፉ ሥራ ጠላት አደረገው እንዳለ ጌታ ሁልጊዜ የሚያለያይ የሚከፋፍል የቤተ ክርስቲያንን አንድነት የሚያናጋ ሥራ ከጠላት ከዲያቢሎስ ነውና አውጥተን ልንጥለው በጎውን ቀናውን የፍቅር የሆነውን ልንይዘው ይገባል:: ዓላማችን ቤተክርስቲያንን ማገልገል ፍጻሜያችንም መንግሥተ ሰማያትን መውረስ ከሆነ አማራጩ ክፉውን ነገር ከመካከላችን አውጥቶ ፍቅርና ሰላምን መመሥረት ብቻ ነው::

በአጠቃላይ ለዚህ የመለያየትና የመጠላላት ከንቱ ፍላጎት ሲባል የቤተ ክርስቲያን አንድነትና የምእመናን ሰላም ፈተና ውስጥ መግባት የለበትም:: ስለሆነም የሚመለከተን ሁሉ ደግ የሆነውን ነገር ከክፉው በመለየት እግዚአብሔር ለሚወደውና ለበለጠው ነገር መሣሪያና ምክንያት ለመሆን የምንተጋ እንጂ በተቃራኒው ሆነን ለቤተ ክርስቲያንም ለሀገርም የሚጎዳ ተግባርን እየፈጸምን የምንገኝ አንሁን:: ክፉውን ሐሳብ የሚለያየንን፣ መንጋውን የሚበትነውን፣ ቤተ ክርስቲያናችንን የሚጎዳውን ለሀገር ለወገን የማይጠቅመውን ክፉ ሐሳብ አውጥተን እንጣለው:: ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ደቀ መዛሙርቱ "ክፉውን ከመካከላችሁ አውጡት" እንዳለው እኛም ክፉውን አውጥተን መልካሙን ይዘን የመንግሥቱ ወራሾች እንድንሆን እግዚአብሔር ይፍቀድልን፤ አሜን::

# ከንቱ ውዳሴ

## ዐውደ ስብከት

*በቀሲስ ዘክርስቶስ ጸጋዬ*

በዚህ ባለንበት በ፳፩ኛው ክፍለ ዘመን ለመዘርዘር የሚያዳግቱ በርካታ ሥጋን ከነፍስ የሚለዩ በሽታዎች አሉ። ምንም እንኳን የበሽታው ዓይነት፣ ደረጃው፣ ምልክቱ እና ዘመኑ ወዘተ… የተለያየ ቢሆንም የመኖሩንና የብዛቱን ጉዳይ ግን የምንጠራጠርበት አይደለም።

በዚህም መሠረት በዚህ ጽሑፍ የምንመለከተው በቤተ ክህነቱም ሆነ በቤተ መንግሥቱ በአጠቃላይ በሀገር ደረጃ እየፈተነ የሚገኝ፣ የሰዎችን መልካም ሥራ ገደል የሚያስገባ፣ የኦርቶዶክሳዊ መንፈሳዊነትን ሕይወት ያለዋጋ እያስቀረ ስላለው"ውዳሴ ከንቱ" ስለተባለው የዘመናት በሽታ ነው። በዚህ በሽታ ያልተለከፈ፣ ያልተጠቃ የለም እስከሚያስብል ድረስ ብሎም የማይድን በሽታ ያልሆነበት ያለ እስከማይመስል ድረስ ብዙዎችን ተቆጣጥሯል።

## ትርጉም

**ውዳሴ፡-** ወደሰ፣ አመሰገነ ከሚል ግስ የተገኘ ሲሆን ምስጋናየሚል ትርጉም ይሰጣል። ውዳሴ ማርያም፣ ውዳሴ አምላክ፤ የማርያም ምስጋና፣ የአምላክ ምስጋና ማለት ነው። ለሰዎች (ለፍጡራን) የሚሰጠውን ምስጋና የሚገባምስጋና እና የማይገባ /የማይጠቅም/ ምስጋና ብለን በሁለት ከፍለን ልናየው እንችላለን።

## የሚገባ ምስጋና (ውዳሴ)

የመጀመሪያው የምስጋና ዓይነት በተሠራ ሥራ፣ በተከወነ ምግባርና ትሩፋት፣ በሚኖረው መንፈሳዊ ሕይወት ማመስገን፣ መመስጋገን ተገቢ እና የሚገባ ምስጋና ነው። አባቶቻችን "ወድሶ ለሰብእ በዘኢኮነ ድልወቱ፤ ሰውን ባልሆነው ነገር እንኳን አመስግነው" ይላሉ። ሳልሠራ ይህን ያህል ምስጋና ያገኘሁ ባደርገውማ (ብሠራውማ) ምን አገኝ ነበር? ብሎ ይበልጥ እንዲተጋ ለማድረግ ሲሹ። ይህ ምስጋና/ውዳሴ/ የሚገባ ምስጋና በመሆኑ ሰጪውንም ሆነ ተቀባዩን ከሚያስመሰግን ውጪ አያስነቅፋቸውም።

በማኅበረሰባችን ውስጥ "እጁ አመድ አፋሽሆነ፣ በልቶካጅ፣ ምስጋና ቢስ፣ የበላበትን ወጭት ሰባሪ …" በማለት አድራጊው ሰው የሚያማርረው የተደረገለት ሰው ባለማመስገኑ፣ በተገቢው መንገድ በሠራው ሥራ መመስገን፣ መበረታታት፣ መሸለም እና እግዚአብሔር ይስጥልኝ መባልን ስለሚፈልግ ነው። የተደረገለትም እግዚአብሔር በሌሎች ሰዎች ላይ አድሮ ስላደረገለት ነገር ማመስገን ተገቢ ነው። ምክንያቱም ገና በጉዞ ላይ ያለን ተጓዦች ነንና ለእግዚአብሔር በሚመችና እንደ ፈቃዱም እንኖር ዘንድ ስለታዘዝን ሁሉ በአግባቡ ሊሆን፣ ሊደረግ ይገባል።

አንዳንድ ሰዎች መልካምሥራ ሲሠሩ መሥራት ስላለባቸው የሚሠሩ፣ ለመመስገን ሳይሆን የተሰጣቸውን ተልእኮ ለማሳካት የሚጥሩ ናቸው። ይሁን እንጂ በዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ ውስጥ የተጣለባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ ሲወጡ፣ ሠርተውም ሲገኙ መመስገናቸው አይቀርም። በሌላ በኩል ደግሞ ለመመስገን ብለው የሚሠሩም አሉ። ስለዚህ የተለያዩ ደረጃዎች እንዳሉ ማስተዋል ይገባናል።

ቅዱሳን አባቶቻችን ምንም እንኳን ከሰው የሚሰጠውን ምስጋና ባይፈልጉትም፤ለእነርሱ የሚገባ የጸጋ፣

የአክብሮት ምስጋና ይሰጣቸዋል፡፡ ይህ ምስጋና ሥጋዊም ሆነ መንፈሳዊ ጉዳትን አያመጣም፤ ምክንያቱም እውነተኛ አምልኮ፣ ውዳሴ፣ ስግደት እና ክብር ከሚሰጠው፤ ምስጋና የባሕርይ ገንዘቡ ከሆነው እግዚአብሔር ጸጋን፣ ውዳሴ እና ክብርን የተቀበሉ ቅዱሳንን ማመስገን እንደሚገባን በመጽሐፍ ቅዱስእና በትውፊት የተመዘገበ ነውና፡፡

ቅዱሳንን የሚያመሰግን፣ መልካም ሥራ የሠሩ ሰዎችን የሚያከብር እርሱ ስላመሰገነ ይመሰገናል እንጂ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ ስለዚህ ገድል የሚጻፍላቸው፣ መልክአ የሚደረስላቸው የቅዱሳንን ቅድስና ተከትሎ የሚሰጥ ውዳሴ ነው እንጂ፣ቅዱሳን ፈልገውት፣ስጡን አመስግኑን፣ መልክአ ድረሱልን፣ ገድል ጻፉልን ብለው አይደለም፡፡ ይህም ቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን የተሰጣትን ሰማያዊ ሥልጣን ተጠቅማ የምትፈጽመው የጸጋ እና የአክብሮት ውዳሴ ነው፡፡ በመሆኑም በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት በሕይወተ ሥጋ ከተለዩ በኋላ ጊዜ ወስዳ፣ መርምራ የምትወስነው ነው፡፡

ቀደምት ቅዱሳን በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ለሚኖሩት ሕይወት የሚስማማ የክብር ስም፣ ምስጋና (ውዳሴ) ሲሰጣቸው እንኳን አይገባንም የማንጠቅም ባሪያዎች ነን የሚሉ በልባቸውም፣ በአፋቸውም፣ አጥብቀው የሚቃወሙ ነበሩ፡፡ /ሉቃ.፲፯፥፲/

## የማይገባ ምስጋና

የማይገባ ምስጋና የምንለው ውዳሴው (ምስጋናው) ለአድራጊው ሊሰጥ የማይገባው፣ በተጋነነና ያልሆነውን ሆነ በማለት የሚቀርብ፣ ጥቅም የሌለው፣ የማያስፈልግ፣ ረብ የለሽ፣ ሰውንም ወደ ማይፈለግ አቅጣጫ፣ ለውድቀት የሚመራ የምስጋና ዓይነት ነው፡፡ ይህ ምስጋና የማይረባ፣ የማይጠቅም፣ ከንቱ ምስጋና በመሆኑ ከንቱ ውዳሴ ይባላል፡፡

ከንቱ የሚለው ቃል “ውዳሴ” ከሚለው ቃል ጋር አብሮ ሲነበብ ወይም ሲነገር በተገቢው መንገድና መጠን ከመሆን አልፎ ለታይታ፣ ለመመስገን፣ ራስን ከፍ ከፍ ለማድረግ፣ ከእኔ በላይ ለጎሳር ነው ለመሰኘት የሚደረግ ስለሆነ ምስጋናውን የማይጠቅም፣ የማይገባ እና ከንቱ ያደርገዋል፡፡ ስለዚህ ይህ የማይገባ ምስጋና እጅግ በጣም ረቂቅ በሆነ ሁኔታ ያለቦታው በመጠቀም ወደ ውዳሴ ከንቱ አድጎ መድኃኒት የሌለው የዘመኑ እና የዘመናት በሽታ ሆኗል፡፡

በዘመናችን ከቤተ ክርስቲያን ቀኖና ውጭ በቤተ ክርስቲያኒቱ ስም ሆነው ብዙ ሕዝብ አስከትለው ሥዕሎቻቸውን አሠርተው፣ መልክአ፣ ገድል አጽፈው የሚሸጡ “አቦ አቦ” እየተባሉ እንዲመሰገኑ፣ እንዲከበሩ የሚፈልጉ፤ ተከታዮችንም ለራሳቸው ያከማቹ፣ እየተከበሩና የማይገባቸውን ምስጋና እና ክብርን እየተቀበሉ ያሉ አንዳንድ ሰዎችን አሁን ባለንበት ዘመን ስንመለከት የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መፋለስ፣ የአገልጋዮች እና የምእመናን አቅጣጫ መሳት እጅጉን ያሳዝናል፡፡

**ቅዱሳንን የሚያመሰግን፣ መልካም ሥራ የሠሩ ሰዎችን የሚያከብር እርሱ ስላመሰገነ ይመሰገናል እንጂ የሚነቀፍ አይደለም፡፡**

# የማይገባ የምስጋና ምንጭ

የከንቱ ውዳሴ ምንጩ ከፍጡራን ሲሆን የዘመናት በሽታ ሆኖ እስከ ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ደርሷል፤ ወደፊትም እስከ ዓለም ፍጻሜ ይዘልቃል። የመጀመሪያው አስገኚ የሐሰት አባት፣ ነፍሰ ገዳይ ተብሎ በወንጌል የተነገረበት ዲያብሎስ ነው። ዲያብሎስ ውዳሴ ከንቱን /የማይገባ ምስጋና/ እንደ ሰበቃ /friction/ ድንጋይና ድንጋይ ሲፋጩ እሳት እንዲወጣ ሐሰትን፣የማይገባ ምስጋናን ከራሱ ለራሱ አፍልቆ ለመጀመሪያ ጊዜ ተግባራዊ ያደረገ ነው።

በዕለተ እሑድ መላእክት በተፈጠሩበት ዕለት መላእክት አንድ ጥያቄ አቅርበው ነበር "መኑ ፈጠረነ ወእምኀበ አይቴ መጻእነ…፣ የፈጠረን ማን ነው? የመጣነውስ ከየት ነው?" ብለው እርስ በእርስ በተነጋገሩ ጊዜ የቀድሞው ሳጥናኤል፤ የኋላው ዲያብሎስ አለቃ ስለነበረ ከፍ ብሎ ሲመለከት ሊመረመር የማይችለውን ፈጣሪውን ማየት ባለመቻሉ፤ ዝቅ ብሎ ደግሞ ቢመለከት እርሱ የሚመራቸው ነገደ መላእክት ሆነው በማየቱ "አነ ፈጣሪሆሙ ለእሉ ፍጡራን…፤ ካለመኖር ወደመኖር በማምጣት የፈጠርኳችሁ እኔ ነኝ" ብሎ በትዕቢት በመናገር ሐሰትን፣ የማይገባ ምስጋና መሻትን አፈለቀ፤ የሐሰት አባትም ተባለ።

ከቅዱሳን መላእክት ጋር ፈጣሪን ከማመስገን ኅብረት ተለየ፤ፈጣሪውንም ለማመስገን እምቢ አለ፤ እርሱም አራተኛ ሁኖ መመስገንን ፈለገ። እግዚአብሔር ግን በዕለተ ዐርብ ሰውን ፈጠረ "ፈጠረ ሰብአ ህየንቴከ….፤ በአንተ ፈንታ ሰውን ፈጠረ" (፫መቃ.፬፥፲) እንዲል።

ዲያብሎስ እኔ ያጣኋትን የክብር ሥፍራ ገነትን እንዴት ያገኛታልበሚል ተናዶ፣ ተበሳጭቶ ቆይቷል። በሥነፍጥረት እንደተገለጠው አባታችን አዳም የቀትር ጸሎቱን እያደረሰ ሳለ እባብ መጥታ "ሰላም ለከ ኦ አዳም ንጉሠ ሰማይ ወምድር፤ የሰማይና የምድር ንጉሥ አዳም ሆይ ሰላም ለአንተ ይሁን" አለችው። እርሱም መልሶ "ፍልጢ አርዌ ምድር፤ ለይተሽ ተናገሪ፤ እኔስ ንጉሠ ምድር ነኝ፣ ንጉሠ ሰማይ ወምድርማ ፈጣሪዩ ነው እንጂ መች እኔ ነኝ፤ አላት" ይላል። (መጽሐፈ ሥነ ፍጥረት ገጽ.፹፫)

አባታችን አዳም የሚገባውን እና የማይገባውን ምስጋና ያውቅ ስለነበረ የሰማይ ንጉሥ መባሉን አጥብቆ ተቃወመ። አዳም ከሔዋን የነበረው አንዱ ልዩነት የሚገባውንና የማይገባውን መለየት መቻሉ እና ለእርሱ የማይገባውን ምስጋና መቃወሙ ነው። እናታችን ሔዋን ግን "ሰላም ለኪ ሔዋን ንግሥተ ሰማይ ወምድር፤ የሰማይና የምድር ንግሥት ሔዋን ሆይ ሰላም ለአንቺ ይሁን" የሚለውን የማይገባውን ሰላምታ፣ ምስጋና እና ስምን ሲሰጣት እንደወረደ በደስታ ተቀበለችው። በዚህም ቀዳዳ አበጅቶ እስከ መጨረሻ ድረስ እጅ አዘርግቶ፣ ቅጠል እስከ መበጠስ አድርሶ፣ ለሞተ ሥጋ፣ ለሞተ ነፍስ ያደረሳቸው ከጥንተ ጠላታችን የተገኘ ጥንተ ጠላት ውዳሴ ከንቱ ነው። ስለዚህም በሔዋን ዘንድ አላዋቂነት እና የውዳሴ ከንቱ ምኞት/ ፍላጎትን/ እንመለከታለን። ብዙ ሰዎችም በዘመናችን ይኸው የምስጋና ዓይነት ያልሆኑትን ናችሁተብለው ከፍ ከፍ ሲደረጉ ሳያስተባብሉ በደስታ የሚቀበሉ አሉ። በመሆኑም ውዳሴ ከንቱ ጥንት ምንጩ ዲያብሎስ እንደሆነም መጻሕፍት ይገልጣሉ።

ከንቱ ውዳሴ የሰው ልጆች አውቀውትም ሆነ ሳያውቁት ብዙዎችን ከጸጋው ዙፋን ያራቀተ፣ ዓላማቸውን ያሳተ፣ አቅጣጫቸውን ያሰናከለ ከባድ የሆነ የበጉ ኀሊና ወጥመድና እንቅፋት ነው። ከንቱ ውዳሴ ያለ እኔ ሰው የለም የሚያሰኝ ትዕቢትንና ትምክሕትን የሚያስከትል ከያዘ የማይነቀል መርዛማ ሥር ነው።

ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ከንቱ ውዳሴ በተለያየ መልኩ ይገልጻሉ፤ አጥብቀውም ይቃወማሉ ሲገልጹትም፡- የረቀቀ የሰዎች ጠላት፣ የድፍረት ኃጢአት አካል፣ ከጥንት ጠላታችን የተገኘ ጥንተ ጠላታችን፣ በፈተና የሚጥል ለትዕቢት የሚጋብዝ ምስጋና፣ የአሕዛብ ተልእኮና ልማድ፣ ንጽሕናን የሚያሳጣ፣ ወዘተ... እና የመሳሰሉትን በማለት ገልጸውታል። ፈሪሳውያን ከጽድቅ ተራቁተው ዋጋቸው በምድር ብቻ ሆኖ የቀረው ራሳቸውን ጻድቅ በማድረጋቸውና የሚሠሩት ለታይታ በመሆኑ ነው። /ሉቃ.፲፰፥፱፤ማቴ.፳፥፪-፲፰/

## የስያሜ ጉዳይ እና ውዳሴ ከንቱ

ከጥቂት ዓመታት በፊት በአንድ አጥቢያ ላይ "ልዩ መርሐግብር ተዘጋጅቶ" አንድ `ታዋቂ` የሚባል ሰው በመርሐ ግብሩ ላይ እንደሚገኝ ስለተነገረ ብዙ ሰው በመርሐ ግብሩ ላይ ታድሟል፤ እኔም ከአንድ ወዳጄ ጋር ተገኝተናል። እንደ አጋጣሚ ታዋቂው መምህር ባልታወቀ ምክንያት ሳይገኝ ቀረ። መርሐ ግብር የሚመራው ላልተገኘው መምህር ለዚያ ሁሉ በጉባኤው ለተሰበሰበ ታዳሚ ከመጠን ያለፈ ማንነት ሰጥቶ፣ አግዝፎና ከእሳቸው ወዲያ ለነሳር ነው በሚል ውዳሴ አዝንቦላቸው መድረኩን ለደብሩ አስተዳዳሪ አስተላለፈ።

የደብሩ አስተዳዳሪም ተነሥተው እያዋዙ የራሳቸውን ታሪክ እየነገሩን እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ተአምር፣ እንዴት ጉዳያቸውን ለማስፈጸም ሲሉ "ኤንባሲ" ሊገቡ የቻሉበትን መንገድ እና ውጭ ሀገር ደርሰው እንዴት እንደመጡ ተረኩልን። ከጨረሱም በኋላ ቀጣዩ መርሐ ግብር የነበረው በእርሳቸው በኩል ለሀገረ ስብከት ባቀረቡት ሐሳብ መሠረት ለደብሩ አገልጋዮች የማዕረግ ስም የያዘ ደብዳቤ መምጣቱንና እርሱም ለእያንዳንዱ እንደሚሰጥ ገልጠው መስጠት ተጀመረ።

ሊቀ ሊቃውንት ....፣ መጋቤ ምሥጢር....፣ መጋቤ... አገሌ ....ሊቀ ትጉሃን ...፣ እየተባለ ከሀገረ ስብከት የመጣው ደብዳቤ እየተነበበ ሲሰጥ ሕዝቡም ደስታውን በጭብጨባ በዕልልታ እየገለጠ ቆየና መርሐግብር ይመራ ለነበረው ተራ ደርሶ ሲሰጠው የተሰጠው ስም "መጋቤ ምሥጢር... አገሌ" ተብሎ ደብዳቤው ተነብቦ ሲሰጥ ምእመኑ አሁንም ደስታውን ገለጠ። ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ጥግ አድርገው፣ ከልጅነት እስከ ዕወቀት በትምህርትና በአገልግሎት ደክመን ስለቸን ሳይሉ የሚያገለግሉትን ማመስገን፣ እንደ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንም የማዕረግ ስም መስጠት ተገቢ ነው። ነገር ግን የማይገባቸው ሲሆን፣ ትምህርት ባልዋለበት ውለው የማይገባቸውን የማዕረግ ስም መስጠት እየተለመደ የመጣ ይመስላል። ከንቱ ውዳሴም ጠልፎ እንዳይጥላቸው መጠንቀቅ፤ ክብር ለሚገባቸውም ክብርን መስጠት ይገባል።

**ከንቱ ውዳሴ የሰው ልጆች አውቀውትም ሆነ ሳያውቁት ብዙዎችን ከጸጋው ዙፋን ያራቆተ፣ ዓላማቸውን ያሳተ፣ አቅጣጫቸውን ያሰናከለ ከባድ የሆነ የበጐ ኅሊና ወጥመድና እንቅፋት ነው።**

ከቅርብ ዘመናት ወዲህ ግን አሁን ባለንበት የሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን አንድ ሰው ሁሉንም መሆን የቻለበት ዘመን እየሆነ በመምጣቱ እጅግ ያሳዝናል። ምንም ያልተማረውን ሊቀ ሊቃውንት፣ የጠብ እና የነገር አባት የሆነውን መልአከ ሰላም፣ በአግባቡ ያልቀጸለውን መጋቤ አዲስ፣ መጋቤ ብሉይ፣ የአበውን ሥርዓት የማይጠብቀውን ይልቁንም የሚያጠፋውን መጋቤ ሥርዓት፣ አቅመ ደካማውን መልአከ ኃይል፣ በጨለማ የሚመላለሰውን መልአከ ብርሃን/መልአከ ብርሃናት/ እየተባለ ነው።

ዛሬ ለመሰየምም ሆነ ለመሰየም ግድ የሌላቸው ብዙ ሰዎች አሉ። ዲያቆን፣ ቄስ፣ ቆሞስ፣ ሊቀ፣ መጋቤ ሐዲስ፣ መጋቤ ሃይማኖት፣ መልአከ መንክራት ወዘተ…እንዲሁ የሚለጠፉ ስያሜዎች ሆነዋል። ቤተ ክርስቲያን ለሚገባቸው ሰዎች ስያሜዎችን ስትሰጥ መስፈርት፣ ትርጉም፣ ምሥጢር እና ደረጃ አላት። (፩ጢሞ.፫፤ ቲቶ.፩፥፯)። ለሁሉ በአግባቡና እንደ ችሎታው መጠን የማዕረግ ስም መስጠት ተገቢ ቢሆንም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ልጆቿ በከንቱ ውዳሴ ተጠልፈው እንዳይጠፉባት የራሱ ተገቢ የሆነ ስያሜ ስላለው በጥንቃቄ ሊከናወን ይገባል።

የስያሜ ጉዳይ ትኩረት የሚሰጠው በመሆኑ የሊቢያን ሰማዕታት "የሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ሰማዕታት" ለማለት በጥድፊያ ሳይሆን በጥሞና ተመልክቶ ነው ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ያስተላለፈው።

**እውነት ያልሆነ ያልተገባ ስያሜ ቁጥሩ ከውዳሴ ከንቱ ነው። ቢጠሩበትም እንኳን ኀሊና ከውስጥ ሆኖ መጠየቁ አይቀርም። የማይመጥን የማይገባ ስያሜና ምስጋና ለራስ ማድረግ  በእርያ አፍንጫ ላይ የወርቅ ቀለበት ማድረግ ነውና አጥብቆ መቃወም ያስፈልጋል።**

በቀኖና ቤተ ክርስቲያንም ለአንድ ኤጲስ ቆጶስ በሢመቱ ጊዜ መጠሪያ ስም የሚሰጠው ቅዱስ ሲኖዶስ ነው። ከዚህ ክብር መውረድና ማውረድ ግን ሕገ ቤተ ክርስቲያንን መጣስ በመሆኑ "ኤጲስ ቆጶሱ ከተሾመበት ቀን ጀምሮ ብፁዕ አባ እገሌ ተብሎ በቅዱስ ሲኖዶስ በሚሰጠው የኤጲስ ቆጶስነት ስም ይሰየማል።" (አንቀጽ፴፮፥፩) እንዳለው። በዚህ መንገድ የተገኘን የከበረ ስምንም ማክበር እንደሚገባ ያዝዛል።

በሌላ መልኩምተገቢ ያልሆነ የሽንገላ ስያሜ በአሁኑ ጊዜ እየተስፋፋ ስለሆነ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።አግባብ ያልሆነ ስያሜ ምስጋናም ለሰጭውም ሆነ ለተቀባዩ ውርደት ነውና፤ሰጭውም ሊጠነቀቅ፣ ተቀባዩም ባልዋለበት ከሆነ እምቢ ማለት ይገባዋል።

እውነት ያልሆነ ያልተገባ ስያሜ ቁጥሩ ከውዳሴ ከንቱ ነው። ቢጠሩበትም እንኳን ኀሊና ከውስጥ ሆኖ መጠየቁ አይቀርም። የማይመጥን የማይገባ ስያሜና ምስጋና ለራስ ማድረግ  በእርያ አፍንጫ ላይ የወርቅ ቀለበት ማድረግ ነውና አጥብቆ መቃወም ያስፈልጋል።

የዘመናት በሽታ የሆነው ከንቱ ውዳሴን በመሸሽ ብዙዎች የማይገባቸውን አይገባንም ብለው የሚሸሹ እንዳሉ ሁሉ የማይገባቸውን ይገባናል በማለት፣ ያልሆኑትን እንደሆኑ አድርገው  ባልዋሉበት ውለናል እያሉ የሚቀርቡ ፍጻሜአቸው በማይድን ከንቱ ውዳሴ በሽታ ተይዞ መኖርና መሞት ነው። ከዚህ ክፉ በሽታ ርቀንና ተጠብቀን የአምላካችን የስሙ ቀዳሾች፣ የክብሩ ወራሾች ሆነን እንድንገኝ በማስተዋልና በጥበብ መንዝ ከእያንዳንዳችን ይጠበቃል።

*ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን!!!*

# በቃልህ አዝዝ ልጄም ይድናል

(ማቴ.፰፥፰)



በዲ/ን ዐቢይ ሙሉቀን

ነቢያት በትንቢታቸው፣ ሐዋርያት በስብከታቸው ሕይወት፣ መድኃኒት እንደሆነ የመሰከሩለት፣ የስሙ ትርጓሜም መድኃኒት የሆነ ሁሉ የሚቻለው አምላክ በመዋዕለ ሥጋዌው በዚህ ዓለም ሲመላለስ በዋናነት ዓለምን የማዳን እና ለዓለም አርአያ የመሆን ተግባራትን አከናውኗል፡፡ ሕሙማነ ሥጋን በተአምራት ሕሙማነ ነፍስን በትምህርት አድኗል፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን በዚህ ዓለም ያከናወነውን ተግባር ሁሉ ጠቅሶ መጨረስ አይቻልም፡፡ በመጽሐፍም ሁሉ ተዘርዝሮ አልተጻፈም፡፡ ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ "ጌታችን ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያልጻፈ ብዙ ሌላ ተአምራት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ፡፡ ነገር ግን ይህ የተጻፈ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እናንተ ታምኑ ዘንድ አምናችሁም በስሙ የዘለዓለም ሕይወትን ታገኙ ዘንድ ነው" (ዮሐ.፳፥፴-፴፩) በማለት እንደመሰከረለት የተጻፈው ጥቂቱ ብቻ ነው፡፡

ጊዜ ገጥሟቸው ከመዋዕለ ሥጋዌው ደርሰው በስብከቱ፣ በተአምራቱ አምነው የዳኑት እጅግ ብዙ ናቸው፡፡ ነገር ግን እርሱ የማዳን ተግባሩን ፈጽሞ በክብር ወደ ባሕርይ አባቱ እና ወደ ባሕርይ ሕይወቱ ካረገ በኋላ እርሱ የሾማቸውን መምህራን ሰምተን፣ የፈጸማቸውን ተግባራት ከመጻሕፍት ተረድተን ዘለዓለማዊ ሕይወትን እንወርስ ዘንድ እግዚአብሔር ባወቀ ለእኛ የሚሆነን ያህል ተጻፈልን፡፡ ሐዋርያትን፣ ሊቃውንትን መምህራንን የሾመልን፣ ከሦስቱ አካል አንዱ ወልድ አካላዊ ቃል በሥጋ ተገልጦ ወደዚህ ዓለም የመጣ፣ ዓለምን ያዳነ የሕይወት ቃል ነው፡፡

ወንጌላዊውና ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ከዋለበት እየዋለ ከአደረበት እያደረ የተማረውንና ያየውን ሲያስረዳ "ንዜንወክሙ በእንተ ውእቱ ዘሀሎ እምቅድም ውእቱ ዘሰማዕናሁ በእዘኒነ ወዘርኢናሁ በአዕይንቲነ ወዘጠየቅናሁ ወዘገሠሥናሁ እደዊነ በእንተ ነገረ ሕይወት፤ ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያ የነበረውንና የሰማነውን በዓይናችንም ያየነውን የተመለከትነውንም እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራለን፡፡" (፩ዮሐ.፩፥፩) በማለት ጽፎልናል፡፡

ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ዓለምን ሊያድን በጠባብ ደረት በአጭር ቁመት ተወስኖ ወደዚህ ዓለም የመጣው ቅድመ ዓለም የነበረ መሆኑን መጀመሪያ የነበረው በማለት ቀዳማዊነቱን አስረዳን፡፡ ይህ ሐዋርያ ወንጌሉን ሲጽፍም " በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ፡፡ ይህም በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡፡ ሁሉም በእርሱ ሆነ፤ ከሆነውም ሁሉ ያለእርሱ ምንም የሆነ የለም" (ዮሐ.፩፥፩-፫) በማለት ቀዳማዊነቱን፣ ሁሉን ቻይነቱን፣ ሁሉን ፈጣሪነቱን ዘለዓለማዊነቱን አስረዳን፡፡ ይህን ቀዳማዊ የሆነውን አምላክ የሕይወት ቃል ብሎታል፡፡ ይህ የሕይወት ቃል ደግሞ ጥንት ፍጥረታትን ሲፈጥር ከብርሃን መፈጠር ጀምሮ ለመላእክት የተሰማ፣ በኋላም ለሰው ልጆች ሁሉ እርሱ በፈቀደው መጠን እየተገለጠ ሲያናግር የተሰማ፣ በኋላም በሥጋ ማርያም ተገልጦ ሲያስተምር በሐዋርያት ጆሮ የተሰማ አምላክ ነው፡፡ ለዚህም ነው በጆሯችን የሰማነውን በማለት የገለጸው፡፡

በነቢያት ትንቢት ይወርዳል ይወለዳል ተብሎ እንደተነገረለት በመለኮቱ ከባሕርይ አባቱ ሳይለይ በተለየ

አካሉ ሥጋ ማርያምን ተዋሕዶ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ በሐዋርያት ዐይን ታየ፣ በእጃቸውም ተዳሰሰ። በመጽሐፈ ኪዳን "ዘውእቱ አምላክ ዘበአማን ዘበነቢያት አቅደመ ተዐውቆ ወበሐዋርያት ተሰብከ ወእመላእክት ተአኰተ ወእምኀበ ኵሉ ተሰብሐ፤ በነቢያት መታወቅን ያስቀደመ፣ በሐዋርያት የተሰበከ፣ በመላእክት የተመሰገነ፣ በሁሉ ዘንድ የተመሰገነ በእውነት አምላክ ነው" (ትምህርተ ኅቡአት) ተብሎ የተነገረለት አምላክ ነው።

ነቢያት አስቀድመው ይወርዳል ይወለዳል ብለው ትንቢት የተናገሩለት፣ ሐዋርያት ወረደ ተወለደ ብለው የሰበኩትና የመሰከሩለት አምላክ መድኃኒት ነው፣ የሕይወት ቃልም ነው፣ ሁሉን ይችላል። ስለዚህ በመቶ አለቃው አንደበትም "በቃልህ አዝዝ ልጄ ይድናል" ተብሎ ተነገረለት። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በልዩ ልዩ መንገድ ሕሙማንን ፈውሷል። ለማሳያ ያህል በሚከተሉት መንገድ እንደፈወሰ እንመለከታለን።

በገሢስ፡- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕሙማንን ዳስሶ እንደፈወሰ ወንጌላዊው ማቴዎስ "ጌታችን ኢየሱስም ወደ ጴጥሮስ ቤት በገባ ጊዜ የጴጥሮስ አማት በንዳድ ታማ ተኝታ አገኛት። እጇንም ይዞ ዳሰሳት፤ ንዳዱም ተዋት፤ተነሥታም አገለገለቻቸው።" (ማቴ. ፰፥፲፬-፲፭) በማለት የጻፈውን የወንጌል ክፍል እናነባለን። ጥንት ዓለምን ሲፈጥር በኀልዮ፣ በነቢብና በገቢር የፈጠረ አምላክ በመዋዕለ ሥጋዌውም በኀልዮም፣ በነቢብም ፣ በገቢርም ፈውሷል። ሁሉ የሚቻለው አምላክ ነውና በሽተኞችን መድኃኒት በሆነው እጁ ሲዳስሳቸው ይፈወሳሉ።

በወሪቀ ምራቅ ፡- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ፣ ዓለምን የፈጠረ፣ ዓለምን ሊያድን ወደዓለም የመጣ ነውና ሁሉ የሚቻለው አምላክ እንደሆነ እንድንረዳ በምራቁ ዕውሩን ፈወሰ። "የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ፤ ይህንም ብሎ በምድር ላይ ምራቁን እንትፍ አለ፤ በምራቁም ጭቃ አድርጎ የዕውሩን ዐይኖች ቀባው። እንዲህም አለው ሂድና በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ....ሄዶም ታጠበና እያየ ተመለሰ።" (ዮሐ.፱፥፭-፯) እንዲል። የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ ያለ አምላክ ብርሃንነቱን እንረዳ ዘንድ በምራቁን ዕውሩን አበራ። እኔ እንዲህ ነኝ ያለ አካል መሆኑን ማረጋገጥ መቻል አለበት። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃን ነኝ ሲል ዕውራንን አበራ፣ መድኃኒት ነኝ ሲል ሕሙማንን ፈወሰ።

ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድም በጾመ ድጓ ድርሰቱ "ከልሐ ዕውር በውስተ ፍኖት ወገሠጽዎ እለ ይመርሕዎ ከመ ያርምም ወአእበየ ከሊሐ እንዘ ይብል ተሣሃለኒ እግዚእየ ወልደ ዳዊት ርድአኒ፤ ዕውሩ በመንገድ ላይ ጮኸ፤ የሚመሩትም ዝም ይል ዘንድ ገሠጹት እሱ ግን የዳዊት ልጅ ሆይ ማረኝ እያለ ዝም ማለትን እንቢ አለ" (ጾመ ድጓ ዘምኵራብ) በማለት የዐይነ ስውሩን ጩኸት መዝግቦልን እናገኘዋለን። ከላይ በወንጌሉም እንዳነበብነው የለመኑትን የማይነሳው የነገሩትን የማይረሳው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምራቁን እንትፍ ብሎ ቀባው ዐይነ ስውሩም ተፈወሰ። የሰዎች ምራቅ በዐይን ላይ ቢተፋ ዐይን ሊያጠፋ ይችላል። ኅሊናም ይጎዳል። እገሌ እኮ ፊቴ ላይ ተፍቶብኝ ሄደ ብለው ሰዎች እርስ በእርስ ይጋጫሉ። በእርግጥም አንድ ሰው ሌላ ሰው ፊት ቢተፋበት ነውር ነው ያስቀይማል። ሁሉ የሚቻለውና ሁሉ መድኃኒት የሆነው አምላክ ግን ምራቁ መድኃኒት ነውና ዕውር አበራ።

በዘፈረ ልብስ፡- ዐሥራ ሁለት ዓመት ሙሉ ባለመድኃኒት አጥታ ስትቸገር የነበረች አንዲት ሴት በመድኃኒትነቱ አምና የልብሱን ጫፍ በነካችው ጊዜ ደሟ ቆሞላት ከሕመሟ መፈወስ ችላለች። ይህንም ወንጌላዊው

ማቴዎስ በቅዱስ ወንጌል "እነሆ ከዐሥራ ሁለት ዓመት ጀምሮ ደም ይፈሳት የነበረች ሴት በኋላው መጥታ የልብሱን ጫፍ ዳሰሰች በልቧም የልብሱን ጫፍ ብቻ የዳሰስሁ እንደሆነ እድናለሁ ብላ አስባ ነበርና ጌታችን ኢየሱስም መለስ ብሎ አያትና ልጄ ጽኚ እምነትሽ አዳነችሽ አላት፤ ከዚያም ሰዓት ጀምሮ ያቺ ሴት ዳነች።" (ማቴ.፱፥፳-፳፪) በማለት መዝግቦታል።

በስሙ አምነው የእርሱን መከራ መስቀል ለመቀበል ወስነው ለአገልግሎት የተሰማሩት ሐዋርያትም በልብሳቸው ጫፍ በጥላቸው ሕሙማንን ሲፈውሱ ኖረዋል። ዛሬም ለእግዚአብሔር ቅርብ የሆኑ አባቶች ሀብተ ፈውስ የተሰጣቸው ቅዱሳን ይኖራሉ። የእነርሱ ግን የጸጋ ነው፤ የእርሱ የባሕርዩ ነው። እርሱ ስሙ መድኃኒት ነው፣ ልብሱ መድኃኒት ነው፤ እጁ መድኃኒት ነው። ሕመምተኛው ግን ያድነኛል ብሎ አምኖ መቅረብ ይኖርበታል። ዐሥራ ሁለት ዓመት ደም ይፈሳት የነበረችው ሴት "እምነትሽ አዳነችሽ" እንዳላት መጻሕፍት ይመሰክሩልናል።

በቃል፡- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከላይ በዘረዘርናቸው ማለትም በመዳሰስ፣ በምራቁ፣ በልብሱ ጫፍ እንደፈወሰ ሁሉ በቃሉም የፈወሳቸው ሕሙማን በርካታ ናቸው። ለምሳሌ ያህል በርእሳችንም መነሻ ያደረግነውን የመቶ አለቃውን ልጅ ታሪክ እንመልከት። ይህን ታሪክ ወንጌላዊው ማቴዎስ "ወአውሥአ ሐቤ ምዕት ወይቤ እግዚኦ ኢይደልወኒ ከመ አንተ ትባእ ታሕተ ጠፈረ ቤትየ ዳእሙ አዝዝ በቃልከ ወየሐዩ ወልድየ፤ የመቶ አለቃውም መልሶ አቤቱ አንተ ከቤቴ ጣራ በታች ልትገባ አይገባኝም ነገር ግን በቃልህ አዝዝ ልጄም ይድናል ፤...(ማቴ.፰፥፩-፲፫) በማለት በቅዱስ ወንጌል መዝግቦት እናገኘዋለን።

የመቶ አለቃው መጥቼ አድንልሃለሁ እየተባለ አንተ መጥተህ ከቤቴ ጣራ በታች ልትገባ አይገባኝም በቃልህ አዝዝ ማለቱ እየለመነው ያለው ሁሉ የሚቻለው አምላክ እንደሆነ በእርሱ ላይ አድሮ ሊያስተምረን ስለፈቀደ ነው። የመቶ አለቃው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቃሉ በማዘዙ እንደሚሆንለት አምኖ ተናገረ። በእርግጥም ሁሉ ይቻለዋል ሊቁ ቅዱስ ያሬድም እንዲህ በማለት ይገልጸዋል።

"ዘወረደ እምላዕሉ አይሁድ ሰቀሉ ወሚመ ኢያእመሩ እግዚአ ኩሉ ዘየሐዩ በቃሉ፤ቅድመ ዓለም የነበረ ዛሬም ያለ ዓለምን አሳልፎ የሚኖር እግዚአብሔር ከላይ ከሰማይ የወረደው ፤አይሁድ ሰቀሉት፤ግን ምንም አላወቁም ሁሉን በቃሉ የሚያድነውን የሁሉን ጌታ ሰቀሉት።" (ቅ/ያሬድ፣ ጾመ ድጓ) በቦታ የማይወሰነው አምላክ ልዕልናውን ለመግለጽ ከላይ የወረደውን ተብሎ ይነገርለታል። ይህ ከላይ የወረደው አምላክ አይሁድ የሰቀሉት፣ የሁሉ ጌታ፣ በቃሉ የሚያድን እነርሱ ግን ያላወቁት አምላክ እንደሆነ ሊቁ ያስረዳናል።

**በስሙ አምነው የእርሱን መከራ መስቀል ለመቀበል ወስነው ለአገልግሎት የተሰማሩት ሐዋርያትም በልብሳቸው ጫፍ በጥላቸው ሕሙማንን ሲፈውሱ ኖረዋል።**

ሊቁ ቅዱስ ያሬድ የራሱን የመቶ አለቃውን ቃልም "ይቤሎ መስፍን ለኢየሱስ በዕለተ ሰንበት ኢይደልወከ ትባእ ታሕተ ጠፈረ ቤትየ አዝዝ በቃልከ ይሕየው ወልድየ፤ መስፍኑ ኢየሱስን በዕለተ ሰንበት እንዲህ አለው ከቤቴ ጣራ በታች ትገባ ዘንድ አይገባህም በቃልህ ብቻ አዝዝ ልጄ ይድናል። (ቅ/ያሬድ፣ ጾመ ድጓ) በማለት ገልጾታል። አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫም "ዐቃቤ ሥራይ ወረደ እምሰማየ ሰማያት ወዕፀ ፈውስ ተረክበት በቤተ ዳዊት፤ ባለመድኃኒቱ ከሰማየ ሰማያት ወረደ ለመድኃኒትነት የምትሆነው እንጨት ከዳዊት ቤት ተገኘች" (መጽሐፈ ምሥጢር) በማለት ያስረዳል። ባለመድኃኒቱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን ለመድኃኒትነት የምትሆነው እንጨት የተባለች አምላክን በኀቱም ድንግልና ፀንሳ በኀቱም ድንግልና የወለደች ድንግል ማርያም ናት። ከእርሷ በተዋሐደው ሥጋ ዓለምን አድኗልና ለመድኃኒትነት የምትሆነው ዕንጨት ከዳዊት ቤት ተገኘች በማለት አስረዳን።

ስለዚህ የመቶ አለቃው ልጁን እንዲፈውስለት የለመነው ቅድመ ዓለም የነበረው፣ ዓለምን የፈጠረው፣ ዓለምን ለማዳን ወደዚህ ዓለም በሥጋ ማርያም የተገለጠው አምላክ ወልደ አምላክ ነው። ይህን ስለተረዳም ከሩቅ መጥቶ መድኃኒት የሆነውንና ሁሉን የሚችለውን አምላክ ለመነው። ፈቃዱም ተፈጸመለት። መተርጉማን እንደሚያስረዱት በዚህ ታሪክ የመቶ አለቃው ሦስት መሠረታዊ ጉዳዮችን አሟልቶ ተገኝቷል። እነርሱም፡-

## ሀ. ሃይማኖት፡-

የመቶ አለቃው በፍጹም ሃይማኖት ያድንልኛል ብሎ መምጣቱ የፈለገውን ከማግኘት ባሻገር ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም አስመስግኖታል። ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ "ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም" (ዕብ.፲፩፥፮) በማለት እንደገለጸው ሃይማኖቱ ፍጹም መሆኑ እግዚአብሔርን አስደስቶታል። ስለዚህ እንደ መቶ አለቃው የፈለግነውን እንድናገኝ፣ እኛም የፈለግነውን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር የፈቀደልንን እንዲሰጠን በሃይማኖት መጽናት ያስፈልጋል።

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብም "ጥበብን ያጣ ሰው ቢኖር ሳይነቅፍና ሳይነፍግ ለሁሉ በልግስና የሚሰጥ እግዚአብሔርን ይለምን፤ ለእርሱ ይሰጠዋል። ነገር ግን አምኖ ይለምን፤ አይጠራጠርም፤ የሚጠራጠር በነፋስ የሚገፋና የሚነዋወጥ የባሕር ማዕበልን ይመስላልና" (ያዕ.፩፥፭-፯) በማለት እንደገለጸው ያለምንም ጥርጥር የሚለምን ሁሉ የፈለገውን ያገኛል፣ ቢታመም ይፈወሳል፣ ቢያጣ ያገኛል፣ ቢያዝን ይደሰታል፤ ቢቸገር ከችግሩ ይወጣል። ግን ያለምንም ጥርጥር መለመን አለበት። ከመቶ አለቃው የምንማረው ይህን ነው።

## ለ. ጥበብ፡-

መቶ አለቃው እርሱ ያለበትን የሥልጣን ደረጃ በምሳሌነት አቅርቦ እኔም እንደአቅሜ አለቃ ነኝ ከእኔ በታች ያሉትን ማዘዝ እችላለሁ። ለእኔ እንዲህ የሚቻል ከሆነ ለአንተማ ሁሉ ይቻልሃል በማለት ነው ጥያቄውን ያቀረበው። ስለዚህ ጉዳዩን ለመግለጽ በጥበብ መጓዙን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እጅግ ወዶለታል። እኛም ሥራችንን በጥበብ ብናከናውን፣ ጉዳያችንን ከእኛ በላይ ለሆነ አካል በጥበብ ብናስረዳ በፍጥነት ችግራችን ይፈታልናል።

ይህ ዘመን በሥጋ ጥበበኞች ነን ለሚሉት ያልተቻላቸው ምልክቱ እንኳን ከቀን ወደ ቀን እየተለዋወጠና እየተቀያየረ የሚያስቸግር በሽታ የተስፋፋበትና ዓለምም የተጨነቀበት ዘመን ነው። ስለዚህ ሃይማኖታችንን አጽንተን እንደመቶ አለቃው ጥበበኛ ሁነን ይህን ክፉ ቀን ማለፍ ያስፈልጋል። ይህን ክፉ ቀን የምናልፍበት ጥበብም የሚገኘው ከራስ ከባለቤቱ ነውና ይህም እንዲሆን "በቃልህ አዝዝ ልጄ ይድናል" እንዳለው ሁሉ

የአንተ ፈቃድ ከሆነ ከመጣው መከራ እድናለሁ ማለት ይኖርብናል፡፡ ጥበቡንም የሚያድል የጥበብ ባለቤት እግዚአብሔር ነውና የእኛን ጥበብ ከእግዚአብሔር ሳናስቀድም በእግዚአብሔር ቸርነት እንደተገለጠልን እያሰብን እና እያመንን የምንችለውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## ሐ. ትሕትና፡-

ራስን ዝቅ አድርጎ ሌሎችን ማክበር፣ ከራስ ይልቅ ሌሎችን ከፍ ማድረግ ነው፡፡ መድኀነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ ደቀ መዛሙርቱን "ለእናንተ ግን እንዲህ አይደለም፤ ከእናንተ ታላቁ እንደ ታናሽ ይሁናችሁ፤ አለቃውም እንደ አገልጋይ ይሁን" (ሉቃ .፳፪፥፳፮) በማለት አስገንዝቧቸዋል፡፡ የመቶ አለቃውም ምንም እንኳን በሀገሩ ገዢ ቢሆንም ወደ ክርስቶስ ሲመጣ ግን ራሱን ዝቅ በማድረግ በፍጹም ትሕትና መጣ፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን መጥቼ አድንልሃለሁ ሲባልም አንተ ከቤቴ ጣራ በታች ትገባ ዘንድ አይገባኝም በማለት ፍጹም ትሕትናውን ገልጾአል፡፡

**ራስን ዝቅ አድርጎ ሌሎችን ማክበር፣ ከራስ ይልቅ ሌሎችን ከፍ ማድረግ ነው፡፡ መድኀነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ ደቀ መዛሙርቱን "ለእናንተ ግን እንዲህ አይደለም፤ ከእናንተ ታላቁ እንደ ታናሽ ይሁናችሁ፤ አለቃውም እንደ አገልጋይ ይሁን"**

ትምህርቱን ከምንጩ የተማረው ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስም በመንፈስ ቅዱስ ለወለዳቸው ምእመናን መልእክት ሲልክ "ርኀሩኆችና ትሑታን ሁኑ" (፩ጴጥ.፫፥፰) በማለት አስረድቷል፡፡ ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድም ምዕራፍ በተሰኘ ድርሰቱ "እስመ በትሕትና ረከበ ልዕልና ወብፁዕ ሚካኤል ዘቦቱ ትንብልና መጽአ ከመ ይዜኑ ሠናየ ዜና፤ ንዑድ ክቡር የሆነ ሚካኤል በትሕትና ክብርን አገኟልና መልካም ዜናን ሊነግር መጣ" በማለት የትሕትናን አስፈላጊነትና የሚያስገኘውን ክብር ያስረዳል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በተዘረዘረው መሠረት በመዳሰስ የፈወሳቸውንም፣ በምራቁ የፈወሳቸውንም፣ በልብሱ ጫፍ የፈወሳቸውንም፣ በቃሉ የፈወሳቸውንም ስንመለከት ከተፈወሱት በኩል የተሟላ ነገር እንደነበር እንገነዘባለን፡፡ እርሱም ሃይማኖት በዋነኛነት ሲሆን ትእግሥት፣ ጥበብ፣ ትሕትና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ እኛም ሃይማኖትሽ አዳነችሽ፣ ሃይማኖትህ አዳነህ፣ እንደወደድህ ይሁንልህ እንደተባሉ ሰዎች በሃይማኖት ጸንተን በጎ ምግባር ሠርተን በእግዚአብሔር ዘንድ እንድንመሰገን፣ ከመጣብን ቸነፈር እንድንድን፣ በቸርነቱ እንዲሰውረን እግዚአብሔርን በቃልህ አዝዝ እንድናለን፣ ፈቃድህ ይሁን እንፈወሳለን ብለን በእምነት ልንጠይቀው ይገባል፡፡ ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክን የኢየሩሳሌምን መጥፋት እንዳያይ ለስልሳ ስድስት ዓመት ያህል የሰወረ አምላክ አምላካችን ነውና ከመጣው ቸነፈር እንዲሰውረን መልካም ፈቃዱ ይሁንልን አሜን፡፡

# ጊዜው ለጽድቅ የምንበቃበትን የምንሠራበት እንጂ ወደ ጥፋት የምንነዳበት አይሁን



*በዲ/ን አሻግሬ አምጤ*

አምላካችን እግዚአብሔር አስጨናቂ መከራ የሚያመጣው ቢቀሰቅስን አልነቃ ስንል ወይም በበረከት ሊጎበኘን ሲፈልግ ነው፡፡ ለነፍሳቸው ድኅነት የሚጨነቁ ብልሆች መከራ የመጣው እኔ ከኃጢአት ወደ ጽድቅ እንድመለስ ነው ብለው ራሳቸውን ያዘጋጃሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መከራ ሲመጣ ሳናልፍ የበለጠ ኃጢአት እንሥራ በማለት ዕለት ዕለት ኃጢአት የሚርባቸውና ለጥፋት የሚዘጋጁ አሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም እግዚአብሔር እንዲህ ብለህ ተናገር ብሎ ልኮኛል ብለው የራሳቸውን ምኞት እየተናገሩ ራሳቸው በኃጢአት ተጨማልቀው ሕዝብ በኃጢአት ላይ ኃጢአት በመጨምር ከእግዚአብሔር እንዲለይ፣ በእግዚአብሔር ቍጣም እንዲጠፋ የሚገፋፉ አሉ፡፡ እንዲህ ብለው ሲናገሩ በቅቻለሁ እያሉን ስለሆነ ቃላቸው እውነት በሆነ፣ መከራውም በራቀ ነበር፡፡

ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረው የተጨነቁት እንደሚረጋጉ እንጂ ሰላማውያን የበለጠ እንዲሸበሩ አይደለም፡፡ ነቢዩ ኤርምያስ እግዚአብሔር ያዘዘውን ለቤተ አይሁድ በተናገረ ጊዜ የሐሰት ነቢያት የእግዚአብሔር ቃል እኛን ዐልፎ በየት በኩል ወደ አንተ መጣ ብለው በድፍረት እስከ መናገር ደርሰዋል፡፡ በዘመናችን የምናየውም በነቢዩ ዘመን የነበሩ አይሁድ ከፈጸሙት ቢከፋ እንጂ የተሻለ አይለይም፡፡ የዘመናችን ክርስቲያን በአካል ከቤተ ክርስቲያን ባይርቅም በመንፈስ ከእግዚአብሔር ቤት እንደሸፈተ፣ አሁንም ቢሆን መከራው እንዳላስተማረው እያየን እየሰማን ነው፡፡ አገልጋዮች ነን የሚሉት እንኳን ሳይቀሩ ከቤተ መቅደሱ ሸፍተዋል፤ የጠቡትን ጡት የነከሱ የበሉበትን ማዕድ የረገጡ ውለታ ቢሶች ሆነዋል፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔርን በጸሎት እንድንማጸነው ዓለምን የሚያስጨንቅ ይህን ወረርሽኝ አስነሣ፡፡ መከራ ሲበዛ ጸጋ እግዚአብሔር መብዛቱን ሁል ጊዜ የምታስተምረው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንኳን ለልጆቿ ላሳዳጆቿ ስትጸልይ ኖራለች፤ ወደ ፊትም እስከ ምጽአት ትጸልያለች፡፡

ቤተ ክርስቲያን ለሚያምነውም ለማያምነውም፣ ለሚገፋትም ለሚደግፋትም ስትጸልይ መኖሯን ለማረጋገጥ የፈለገ ሰው የምታደርገውን ቀርቦ ማየት ይችላል፡፡ ባሕርይዋን የማያውቁ ወገኖች ሰሞኑን የጸሎት ዐዋጅ መነገሩን ሰምተው ቤተ ክርስቲያን ጸሎት መጸለይ የጀመረችው ዛሬ ይመስላቸዋል፡፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ግን ስለ ሀገር ሰላም፣ ስለ ሕዝብ ደኅንነት ጸሎት ምህላ የጀመረችው በዓለመ መላእክት ከነበረችበት ጊዜ አንሥቶ ነው፡፡ የሰሞኑ ጸሎት ያስገኘላት ጥቅም ቢኖር ሳያውቋት የኖሩት ወገኖቻችን ቅድስናዋን እንዲረዱ ማድረጉ ብቻ ነው፡፡ በአገር ላይ መከራ ሲመጣ አበስኩ ገበርኩ በማለት ጥፋቱ የመጣው በእኔ ኃጢአት ነው ሲል የተሰማ የለም፡፡ ሁሉም ጣቱን የሚቀስረው ወደ ሌላው ነው፡፡ እንደ ሰዶምና ገሞራ ሰዎች፣ በቅዱሱ አባት በኖኅ ዘመን እንደነበሩት ሰብአ ትካት ኃጢአት እየፈጸሙ ኃጢአት የሚናፍቃቸው እንጂ ለንስሓ ለጽድቅ የሚነሡ አልታዩም፡፡ በሽታው በእግዚአብሔር ቍጣ ባይመጣ እንኳ ጸሎት የማያርቀው ደዌ ባለመኖሩ አጥብቆ በመጸለይ የከፋ ጉዳት እንዳያደርስ ማድረግ ይጠበቅብን ነበር፡፡

ሕዝቡን ከእግዚአብሔር በመለየት ከቤተ ክርስቲያን አስኮብልለው በራሳቸው ዙሪያ እየሰበሰቡ ከእግዚአብሔር ጋር እናገናኛችኋለን በማለት የሚቀልዱ ወገኖች የዘመናችን የቤተ ክርስቲያን ፈተናዎች ናቸው፡፡ በስሙ

የቀለዱት የደረሰባቸውን መጥፎ ግብር እየተናገሩ ዛሬም አንድ ጊዜ መድኃኔዓለም ለእገሌ ነገረው፣ ሌላ ጊዜ ለአባ እገሌ እንዲህ አለው፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሌላ እያሉ ሕዝብ እንዲሸበር ያደርጋሉ። ጭንቅና መከራ ሲበዛ ክርስቶስ እዚህ አለ ቢሏችሁ እንኳ እንዳትቀበሏቸው በሚለው አምላካዊ ቃል ስንመራ ብንኖርም ሕይወታችን ባለመለወጡ ነቢያተ ሐሰት የተናገሩትን ሰምተን እንጨነቃለን። በልዩ ልዩ ስልት ሰውን የሚያስፈራሩ፣ በገሃነም እሳት ትለበለባላችሁ የሚሉ የጥፋት መልእክተኞች ሕዝብ በማሸበር ደስታ ለማግኘት ይሞክራሉ። በዚህም የመጣው ሁሉ ወደ ፈለገው የሚነዳን እየሆንን ነው። ጸንታችሁ ቁሙ የተባልነው በእንደዚህ ዓይነቱ ዘመን ቢሆንም ፈርተን የምናስፈራ ብዙዎች ነን።

የፈራውን ወገናቸውን የበለጠ የሚያስጨንቁ፣ የሰውን ሰቆቃ ካልሰሙ ምግብ የማይበላላቸው የጥፋት መልእክተኞችን ልናውቅባቸው ይገባል። ለሁሉ ነገር መፍትሔው በንስሐ ተመልሶ ቅዱስ ቊርባንን መቀበል፣ አምላካችን እንዲምረንም መማጸን ነው። እንዲህ እያደረግን ከአቅማችን በላይ የሆነውን ለአምላካችን ትተንና ምልክት ማየት ሳያስተን ሞት ቢመጣም ተዘጋጅተን እንጠብቅ። በሞተ ሥጋ ላይ ሞተ ነፍስ ሊያስፈርዱብን እንቅልፍ የሚያጡ ነቢያተ ሐሰትን፣ ክህናተ ጣዖትን እኛስ አምላካችንን እናውቀዋለን ከፊታችን ገለል በሉልን በማለት አሳፍረን ልንመልሳቸው ይገባል።

ለክርስቲያኖች ፈተናዎች የሆኑት እነዚህ ብቻ አይደሉም። ኮሮና ቫይረስ ይበልጥ እንዳይሰራጭና ብዙ ሰው እንዳይጎዳ ከቤታችሁ ዋሉ፣ ከሰው አትገናኙ ቢባሉ ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱ የራሳቸውን ሴት ሕፃናት ጭምር በመድፈር ሞት ሆይ ወዴት ነህ ብለው ሞተ ነፍስን የሚጠሩ እየበረከቱ መምጣታቸው ሌላው ችግር ነው። እንዲህ ዓይነት ሰዎች በሽታው በመጥፋት ፈንታ እየተስፋፋ፣ የእግዚአብሔር ቊጣ ወደ ትዕግሥት በመመለስ ፈንታ የበለጠ እንዲያጠፋን የሞትን ሽተል የሚያሸቱ ናቸው።

በአንድ ወቅት ያልፈጸሙት የኃጢአት ዓይነት የለም የሚባልላቸው አንድ ሰው በአንድ አገር ይኖሩ ነበር። እኚህ ሰው ዕድሜ የማያስተማራቸው፣ በሽታ መስመር የማያስገባቸው ነበሩ። በዕድሜያቸው ላይ አንድ ቀን ቢጨመርላቸው ለድኅነት ሳይሆን ለጥፋት ለመጠቀም ለምኞታቸው ገደብ የሌላቸው ሰው ነበሩ። እኚህ ሰው ሲተኙ ክፋት፣ ሲነቁ ኃጢአት በዓይናቸው ይዞራል። ለሰዎች የድኅነት ምክንያት የማያሳጣው አምላካችን እግዚአብሔር መልአከ ሞትን በገሃድ እንዲታያቸው አደረገ። ሁል ጊዜ ኃጢአት የሚያየው ዓይናቸው አንድ ቀን የቤታቸውን በር ከፍቶ ወደ እሳቸው ከሚመጣ መልአከ ሞት ጋር ተገጣጠመ።

**ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረው የተጨነቁት እንደሚረጋጉ እንጂ ሰላማውያን የበለጠ እንዲሸበሩ አይደለም።**

አመጣጡና ግርማው ያስፈራቸው አረጋዊም በደመ ነፍስ “አንተ ማን ነህ” በማለት እየተርበተበቱ ጠየቁት፡፡ “እኔ መልአከ ሞት ነኝ” ሲላቸው ፈጽሞ ደነገጡ፡፡ እየተንቀጠቀጡ “ለምን መጣህ?” አሉት፡፡ እሱም “ኃጢአት ሠርተህ የማይበቃህ በመሆንህ ልወስድህ ነው” አላቸው፡፡ ሽማግሌውም “ስላልተዘጋጀሁ እባክህ ተወኝ፡፡ የአምላኬን ፊቱን እንዴት አየዋለሁ?” በማለት ወሸከቱ፡፡ መልአከ ሞትም “አምላክህ ረጅም ዕድሜ ቢሰጥህም አትማርም፡፡ የምታውቃቸው ከአጠገብህ በሞት ሲወሰዱ አልነቃህም፡፡ መማር የማትፈልግ በመሆንህ ልውሰድህ” ሲላቸው “ከዛሬ ጀምሮ እዘጋጃለሁ የዛሬን ተወኝ” አሉት፡፡ እሱም “እንደማትማር ቢያውቅም አምላክህ አንድ ዕድል ይሰጥሃል” አላቸው፤ እሳቸውም ትንሽ ተረጋጉና ትንፋሻቸው መለስ ብላ “ተመስገን” አሉ፡፡

“ልብ አድርግ ከእንግዲህ ተመልሼ ስመጣ ሌላ ዕድል አልሰጥህም” አላቸው፡፡ እሳቸውም “ከመምጣትህ በፊት አሳውቀኝ እንጂ ግድ የለም እዘጋጃለሁ” ብለውት ሔደ፡፡ ከጥቂት ቀናት በኋላ ከመኖሪያ ቤታቸው ራቅ ካለ ቦታ ሰው መሞቱን ሲሰሙ “ወይ ጉድ” አሉ፡፡ “ሳልነግርህ አልወስድህም ብሎኛል” እያሉ በጥፋት ላይ ጥፋት ጨመሩ፡፡ ሞት እየቀረበ መጥቶ ካጠገባቸው አንድ ሰው ወሰደ፡፡ እሳቸውም አይጉድ ብለው በቀደመ የጥፋት ግብራቸው ቀጠሉ፡፡ አሁንም ቀረብ ብሎ ወዳጃቸውን ወሰደ፤ ከዚያም ልጃቸውን ሲወስድ አልቅሰው ወደ ኃጢአት ተመለሱ፡፡ ከዚያ ሚስታቸውን ወሰደ፡፡ ሌሎችን ሲወስድ ይማራሉ ብሎ ቢጠብቃቸው ወይ ፍንክች አሉ፡፡

መጨረሻ ላይ የቤታቸውን በር ከፍቶ ሲገባ ደነገጡና “አንተ ማንነህ?” ሲሉት “መልአከ ሞት ነኝ” አላቸው፡፡ “ሳልነግርህ አልመጣም ብለኸኝ እኮ ነበር” አሉት፡፡ እሱም “ከዚያ ማዶ ጀምሬ ሰው ስወስድ ተዘጋጅ ማለቴ ነበር፡፡ አንተ ግን ባለፈው እንደነገርኩህ ኃጢአት እየጣፈጠህ ስለሔደ ከዚህ በላይ ዕድሜ ቢጨመርልህም አትማርም፡፡ ተጨማሪ ሰዎችን ሳትጎዳ ልውሰድህ” ብሎ አንቆ ወሰዳቸው፡፡ በዚህ ዘመን የምንገኝ ሰዎችም ኃጢአት ሲርባቸው እንደኖሩት አረጋዊ ነን፡፡ ወደ እሱ እንድንመለስ አምላካችን እግዚአብሔር ልዩ ልዩ ምልክቶችን ቢያሳየንም ከእሱ የሚያርቀንን እንጂ ወደ እሱ የሚያቀርበንን በጎ ተግባር መፈጸም አልቻልንም፡፡ የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ዓለምን ማስጨነቁን ተከትሎ የሰው ዘር በበሽታው እንዳያልቅ ተሰግቶ ከቤታችሁ ዋሉ ብንባባልም በኃጢአት ላይ ኃጢአት እየደረቡ ሞትን በመፈታተን ላይ ያሉ ወገኖቻችን ቊጥር ከመቀነስ ይልቅ እየበዛ መጥቷል፡፡ ከልቡ ታገሡኩ ተመለስኩ የሚል ባለመኖሩ የመከራው ጊዜ እየተራዘመ መሔድ ብቻ ሳይሆን ሌሎች አስጨናቂ ነገሮችም ለመከሠት ምልክቶች እየታዩ ነው፡፡

ከኃጢአት ሁሉ የከፋው ደግሞ የራሳቸውን ሴት ልጆች ደፍረው ቅስማቸውን የሰበሩ ወገኖቻችን እየበዙ መምጣታቸው የብዙኃን መገናኛዎች የውይይት አጀንዳ መሆኑ ነው፡፡ ለራሳቸው ደስታ ብቻ በማሰብ ወይም ተያይዞ ለማለቅ የልጆቻቸውን ቅስም ሰብረው ተስፋቸውን የሚያጨልሙት ሰዎች ቊጥር መብዛት ለተጨማሪ መቅሰፍት ይዳርጋል እንጂ አምላካችን እንዲምረን የሚያራራው ድርጊት አይደለም፡፡ የወገኖቻችን ድርጊትም ሆነ ብዙዎቻችን እየሠራን ያለነው እግዚአብሔር ምሕረት እንዲያወርድ የሚያደርግ ሳይሆን “አሕዛብስ ቤተ አይሁድ ካደረጉት የከፋ ምን አደረጉኝ” በማለት ለሰባ ዓመታት በባቢሎን ተማርከው አሳራቸውን እንዲያዩ እንዳደረጋቸው እኛንም ለተጨማሪ መከራ የሚዳርገን ነው፡፡ “እግዚአብሔር በሰጣቸው የመንግሥት አስተዳደር ላይ የቸልታ መንፈስ ቢያመጡ፣ ሕጉን ቢለውጡ፤ ወሰን ክልላቸውን፣ ትምህርተ ሃይማኖታቸውን ባይጠብቁ፤ የአምላካቸውን፣ የአገራቸውን ክብር ቢንቁ፤ ፍርድ ቢያደሉ፣ መማለጃ ቢበሉ፣ በቤተ መንግሥት፣ በቤተ ክህነት የሚሠራውን ግፍ እንዳያዩ ዐይናቸውን ቢሸፍኑ፣ የድኾችን ጩኸት እንዳይሰሙ ጆሮዋቸውን ቢደፍኑ፤ የግል ጥቅማቸውን ፈላጊዎች፣ መብል መጠጥ ወዳጆች ቢኾኑ፤ የእግዚአብሔርን አደራ ቢያቃልሉ፣ አፈ ጻድቅ መስለው በልቡናቸው ቢክዱ፣ በእርሱ ላይ የሰው ወይም የጋኔን ውሽማ

ይዘው ጉድን ጉድን ቢሔዱ፤ ከቤት ወይም ከጎረቤት ጠላት አስነሥቶ ያስደነግጣቸዋል፤ ያንቀጠቅጣቸዋል፡፡ ከክብራቸው፣ ከቤታቸው ያወጣቸዋል፡፡ በደዌ፣ በጦር፣ በረኃብ፣ በቸነፈር፣ በስደት፣ በሞት ይቀጣቸዋል” (አለቃ አያሌው ታምሩ፣ ፲፱፻፺፩ ገጽ፻፴) በማለት ሊቁ የተናገሩት እየተፈጸመብን ነው፡፡

መልአከ ሞት ከዚህ በላይ እንዴት ልታገሥህ በማለት ተማሮ ሊቆርጠን እንዲመጣ የሚያደርገው እንዲህ ዓይነቱ ኃጢአትን ባለመጥገብ በጥፋት ላይ ጥፋት ለመፈጸም መነሣሣታችን ነው፡፡ ስንሓ እንድንገባ በወገኖቻችን ሞት ቢነግረንም አልሰማነውም፡፡ ዘር፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ሥልጣን፣ ሀብት እና ሌላም ቊሳዊ ነገር ከማያግደው በሽታ የበለጠ መምህር ሊመጣልን እንደማይችል ተረድተን ለወገኖቻችን ፈተና ከመሆን ፈውስ ለመሆን በስሜት ከመነዳት እንታቀብ፡፡ እንደ ነዌ ከሙታን ተነሥቶ ያልመጣ ካላስተማረን አንመለስም እያልን በኃጢአት ላይ ኃጢአት እየፈጸምን በመሆኑ ኃጢአት መሥራት አንገሽግሾን የእግዚአብሔርን ምሕረት እንለምን፡፡ ማርያም እንተ ዕፍረት ኃጢአት አማናዊውን ደስታ እንደማያስገኝ ተረድታ ወደ ክርስቶስ ስለቀረበች ስሟ ወንጌል በተነበበት ሁሉ ሲጠራ ይኖራል፡፡ አመንዝራዎች ግን ስማቸው በአንድ ትውልድ ይጠፋል፡፡

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በሰሙነ ሕማማት በትምጸልየው ጸሎት “በዚች ቦታና በሌሎችም ቦታዎች ስለሚገኙ፣ በነፍስ በሥጋ ስለታመሙ አባቶቻችንና ወንድሞቻችን ጸልዩ፡፡ ጌታ ለእኛም፣ ለእነሱም ጤንነቱን ሰጥቶ በጎ ነገርን ያደርግልን ዘንድ፡፡ የእኛንም ኃጢአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ፡፡ በባሕር፣ በየብስ፣ በቀላይ፣ በአየር በሌላም መንገድ ሁሉ ስለሚጓዙ አባቶቻችንና ወንድሞቻችን ጸልዩ፡፡ ጌታ በቀና መንገድ መርቶ በሰላም፣ በደስታ ወደ መኖሪያቸው ይመልሳቸው ዘንድ፣ የእኛንም ኃጢአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ፡፡ ከእርሻ ስለሚገኝ ፍሬ፣ ስለዛፎችና ስለወይኖች፣ በዓለም ፍሬን ስለምታፈራ እንጨት ሁሉ ጸልዩ፡፡ ጌታ ባርኮ፣ አብዝቶ፣ ከጥፋትም ጠብቆ ለፍጻሜ ፍሬ ያደርሳቸው ዘንድ፣ የእኛንም ኃጢአታችንን ያስተሰርይልን ዘንድ፡፡ አምላካችን ክርስቶስ በገዥዎችና በፈራጆች ፊት ይቅርታንና ምሕረትን እንዲሰጠን፣ ልቡናቸውንም ሁል ጊዜ በቸርነቱ እንዲያራራልን ጸልዩ፡፡ የእኛንም ኃጢአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ” (ግብረ ሕማማት) በማለት ለሌሎች ብቻ ሳይሆን ለራሷም ትጸልያለች፡፡

**ከኃጢአት ሁሉ የከፋው ደግሞ የራሳቸውን ሴት ልጆች ደፍረው ቅስማቸውን የሰበሩ ወገኖቻችን እየበዙ መምጣታቸው የብዙኃን መገናኛዎች የውይይት አጀንዳ መሆኑ ነው፡፡**

ይህ ብቻ ሳይሆን “በክርስቶስ አምነው ከዚህ በፊት ስለሞቱ ወንድሞቻችንና አባቶቻችን ጸልዩ፡፡ እነሱም፡- የተቀደሱ አባቶቻችን ሊቃነ ጳጳሳትና አባቶቻችን ጳጳሳት፣ አባቶቻችን ኤጲስ ቆጶሳት፣ አባቶቻችን ቆሞሳት፣ አባቶቻችን ካህናት፣ ወንድሞቻችን ዲያቆናት፣ አባቶቻችን መነኰሳትና አባቶቻችን

ሕዝባውያን፣ ሌሎችም ከክርስቲያን ወገን በሞት ያረፉት ሁሉ ናቸው። ጌታ ዕረፍተ ነፍስን ይሰጣቸው ዘንድ ጸልዩ። የክርስቲያን እምነት ላልተፈጸመላቸው ወገኖች ጸልዩ። ጌታ ይባርካቸው ዘንድ፣ እስከ መጨረሻዪቱም ሕቅታ በቀናች ሃይማኖት ያጸናቸው ዘንድ፣ የእኛንም ኃጢአታችንን ያስተሰርይልን ዘንድ። ሐዋርያት ስላጸኗትና ስለሰበሰቧት ስለአንዲት ቤተ ክርስቲያን ሰላም ጸልዩ። ስለሕዝቡም ሁሉ መዳንና ስለቦታውም መጠበቅ፣ የእኛንም ኃጢአታችንን ያስተሰርይልን ዘንድ። ስለአገራችን ኢትዮጵያ፣ ስለአስተዳዳሪዎቿና በጠረፏ ጠላትን በመከላከል ያሉትን ጌታ በሰላም ይጠብቃቸው ዘንድ፣ በዓለሙ ሁሉ ስለአሉ አብያተ ክርስቲያናትም መልካም ነገርን ያስቡ ዘንድ፣ ኃጢአታችንንም ያስተሰርይልን ዘንድ ጸልዩ" (ግብረ ሕማማት) በማለት ስለሰው ልጆች ሁሉ ወደ ፈጣሪዋ ዕለት ዕለት ታሳስባለች። አመኑም አላመኑም ስለ መንግሥታት የምትጸልየው ለፍጥረታት ሁሉ ድኅነት ስለምታስብ ነው።

እንዲህ ዓይነቱ ጸሎት በአንድ በኩል እኛ ኃጢአትን በጽድቅ ለማሸነፍ ትንሣኤ ልቡና እንዲኖረን ሲያደርግ በሌላ በኩል ደግሞ ለሚደግፏት ብቻ ሳይሆን ለሚገፏትም አጥብቃ ፈጣሪዋን የምትማጸን ፍጽምት መሆኗን እንድንረዳ ዓይነ ልቡናችንን ያበራልናል። በአጸደ ነፍስ ላሉት ሳይቀር ጸሎት የማያስፈልገው ፍጡር አለመኖሩንም ያስገነዝበናል። በሯ ላይ ቆመው ቤተ ክርስቲያን እንድትዘጋ የሚያደርጉትንም በፍቅሯ ማሸነፍ እንደምትችል አምና ዕለት ዕለት መሠረቷና ጉልላቷ ወደ ሆነው ክርስቶስ ታሳስብላቸዋለች። በቃል መናገር ብቻ ሳይሆን የተናገረችውን በተግባር ፈጽማ ታሳየናለች። "ይህ ዓይነት አብሮ አደግ ጋኔን ካለጾምና ካለጸሎት አይወጣም" (ማቴ.፲፯፥፳፩) ተብሎ በቅዱስ ወንጌል እንደተነገረው በአገራችንም፣ በዓለማችንም የተከሠተው መቅሰፍት ያለጸሎት ስለማይከስም እንደ አንድ ልብ መካሪ፣ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነን የአምላካችንን ምሕረት መማጸን ሲገባን እባክህ ፈጥነህ አጥፋን ብለን መገዳደር የጀመርን አስመስሎብናል። "የሆድህ ፍሬ፥ የምድርህም ፍሬ፥ የላምህም ርቢ፥ የበግህም ርቢ ርጉም ይሆናል። አንተ በመግባትህ ርጉም ትሆናለህ፥ በመውጣትህም ርጉም ትሆናለህ። እኔን ስለ ተውኸኝ፥ ስለ ሥራህ ክፋት፥ እስክትጠፋ ፈጥነህም እስክታልቅ ድረስ በምትሠራው ሥራ ሁሉ እግዚአብሔር መርገምን፥ ሽሽትን፥ ተግሣጽን ይሰድድብሃል። እግዚአብሔር ትወርሳት ዘንድ ከምትገባባት ምድር እስኪያጠፋህ ድረስ ቸነፈርን ያጠብቅብሃል። እግዚአብሔር በክሳት፥ በንዳድም፥ በጥብሳትም፥ በትኵሳትም፥ በድርቅም፥ በዋግም፥ በአረማሞም ይመታሃል፤ እስክትጠፋም ድረስ ያሳድዱሃል። በራስህም ላይ ሰማይ ናስ ይሆንብሃል፥ ከአግርህም በታች ምድሪቱ ብረት ትሆንብሃለች። እግዚአብሔር የምድርህን ዝናብ ትቢያና አፈር ያደርጋል፤ እስክትጠፋ ድረስ ከሰማይ ይወርድብሃል። እግዚአብሔር ከጠላቶችህ ፊት የተመታህ ያደርግሃል፤ በአንድ መንገድ ትወጣባቸዋለህ፥ በሰባት መንገድ ከእነርሱ ትሸሻለህ፤ ለምድርም መንግሥታት ሁሉ ድንጋጤ ትሆናለህ። ሬሳህ ለሰማይ ወፎች ሁሉ ለምድርም አራዊት መብል ይሆናል፥ የሚያስፈራቸውም የለም፤ እግዚአብሔር ፈውስ በሌለው በግብፅ ቍስል በእባጭም በቋቁቻም በችፌም ይመታሃል፤ እግዚአብሔር በዕብደት፥ በዕውርነት፥ በድንጋጤም ይመታሃል"(ዘዳ፳፰፥፲፰-፳፰) ተብሎ የተነገረው ተፈጽሞብን መዘባበቻ እንዳንሆን እንጠንቀቅ።

ክርስቲያኖች በየአቅጣጫው የሚሰማውን ክፉ ወሬ መቋቋም ተስኗቸውና ግራ ተጋብተው መፍትሔ እንድንሰጣቸው ይጽፋሉ። በእውነቱ ከዚህ ዘመን በላይ ቤተ ክርስቲያን አስተምራ አታውቅም። በአሁኑ ጊዜ እያስተማረችውና እየተናገረችው ካለው ቃል ሌላ ምን ትንገረን? ከመጋቢት ፳፰ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም ጀምሮ በምሕላው፣ በትምህርቱ ፣ በሕማማት ደግሞ በምንባባቱ ካስተላለፈችው ደብቃ ያስቀረችው የለም። እየተነገረ ያለው ካላጽናናን ምን ሊያጽናናን እንደሚችል ርግጠኛ መሆን አይቻልም።

በቴሌቪዥን፣ በጡመራ መድረክ፣ በዩቲዩብ ቃለ እግዚአብሔር ሲተላለፍ አእምሯችንን ሰብስበን ከማዳመጥ ይልቅ በየማኅበራዊ ሚዲያው በሚደመጡ ዋልታ ረገጥ ሐሳቦች ጭቅጭቅ እናሳልፋዋለን። የሚያረጋጋን ለሌሎች ብለን መስማት ሳይሆን ለራሳችን ብለን መስማት ነው። ትምህርቱንም፣ ጸሎቱንም አእምሯችንን ሰብስበን እንከታተል። ቀስ በቀስ የምንሰማው ቃለ እግዚአብሔር ራሳችንን እየለወጠን ይሔዳል። እኛ ሌሎችን ማረጋጋት ሲገባን እየተሸበርን ሌሎችንም ላለማሸበር በያለንበት እንጽና። አምላካችን መጽናናቱን እንዲሰጠን እንማጸነው። እየተማርነው ካለው የበለጠ ማረጋጊያ ቢኖር በነገርናችሁ ነበር። እንድንጠቀም ሆነን ቃሉን እንስማና ለቃሉ የታመነው አምላክ የሚያደርገውን በትዕግሥት እንጠብቅ።

**ክርስቲያኖች በየአቅጣጫው የሚሰማውን ክፉ ወሬ መቋቋም ተስኗቸውና ግራ ተጋብተው መፍትሔ እንድንሰጣቸው ይጽፋሉ። በእውነቱ ከዚህ ዘመን በላይ ቤተ ክርስቲያን አስተምራ አታውቅም።**

የጸሎት ዐዋጁ ቤተ ክርስቲያን ሳትፈጽመው ኖራ የምትፈጽመው አዲስ ነገር ባይጨምርላትም ያላወቋት እንዲያውቋት፣ በየዋህነት የእኔ እገሌ ብለው ሲርቋት የነበሩ ወገኖች የእኛ ብለው እንዲቀርቧት አድርጓል። ከዚህ የተለየም ሌላ ዓላማ ለቤተ ክርስቲያን የላትም። የሰውን ልጅ ከማዳን የበለጠ ተልእኮ አልተቀበለችምና። ሚሲዮናውያን የሃይማኖት ጭምብልን ለብሰው (ሃይማኖተኛ መስለው) ሕዝብን ሲያምታቱ የኖሩበት ድብቅ ዓላማቸው ሰሞኑን ተገልጧል። የራሳቸውን ሃይማኖት ማስተማር ሲሳናቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ማጥላላት ዋና ተግባራቸው ነበርና። እሷ እኮ የእነ እገሌ እንጂ የእናንተ አይደለችም። የእናንተ ብትሆን ኖሮ በቋንቋችሁ ታስተምራችሁ ነበር በማለት እያታለሉ ሕዝባችን የሚሉትን ከድኅነት ነጥለውት ኖረዋል።

እስከ አሁን ወንጌል ይሰበክባቸው ከነበሩ ሦስት ቋንቋዎች ማለትም አማርኛ፣ ኦሮምኛና ትግርኛ በተጨማሪ በወላይትኛ፣ በጋሞኛ፣ በጉራጌኛ፣ በሶማሌኛ ወንጌል ሲሰበክ ሰማን። ዛሬም በሲዳምኛ ቋንቋ ትምህርት ሲሰጥ አደመጥን። ቤተ ክርስቲያን ስንዱ እመቤት በመሆኗ በሁሉም ቋንቋ ማስተማር እንደምትችል የሰሞኑ አገልግሎት በቂ ማሳያ ነው። ይህ ወቅት ቤተ ክርስቲያናችን በልዩ ልዩ ቋንቋዎች ማስተማር የሚችል የተማረ የሰው ኃይል እንዳላት ያሳየችበት፣ ሥርዐተ ጸሎቷ በአሕዛብ ጆሮ የተደመጠበት ወቅት ሆኗል። እንዲህ ያለው ተግባር ዛሬ የተጀመረ ባይሆንም ከትናንቱ የራሱ ታሪክ ተቀያይሞ ከብዙኃን መገናኛ የሚያገኘውን ብቻ ዕውቀት ብሎ የያዘውን የዘመናችንን ትውልድ "እንዲህም አለ እንዴ" እንዲል አድርጎታል። ምክንያቱም ይህ መጥፎ የዘመን ክሥተት (ኮሮና) ባይከሠት ይህ ሁሉ የቤተ ክርስቲያን መክሊት ተገልጦ እንደማይታይም አፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል። ኮሮና ተደብቆ የኖረው የቤተ ክርስቲያን መክሊት እንዲገለጥ፣ ከእንቅልፍ እንድንነቃ እግዚአብሔር ያመጣው ከኃጢአት መመለሻ ጨንገር መሆኑን አምነን ወደ ጽድቅ እንመለስ። በዚህም ሁሉ በመከራውም ሆነ በደስታው ለጽድቅ የምንበቃበትን የምንሠራበት እንጂ ወደ ጥፋት የምንነዳበት አይሁን እንላለን። ወስብሐት ለእግዚአብሔር፣ ወለወላዲቱ ድንግል፣ ወለመስቀሉ ክቡር። አሜን!!

# ክብረ ክህነት

## ክፍል አንድ



*በዲ/ን ዐቢይ ሙሉቀን*

## መግቢያ

"ቤተ ክርስቲያን አካለ ክርስቶስ ወይም ቤተ ክርስቲያን ልትባል የምትችለው ቢያንስ አራት ነገሮን ከራሱ ከክርስቶስ ከተማርነውና ከሐዋርያት ባገኘነው ላይ ብቻ ጠብቃ ስትገኝ ነው። እነዚህም ሐዋርያዊ ትውፊት፣ ሐዋርያዊ ትምህርት፣ ሐዋርያዊ ክህነትና ሐዋርያዊ ሥርዓተ አምልኮን ጠብቃ ስትገኝ ነው። ትምህርቱና ትውፊቱ ለሥርዓተ አምልኮ መሠረቶች ናቸው። ክህነቱ ደግሞ የአምልኮቱ መፈጸሚያ ነው። ያለ እውነተኛ ሃይማኖትና ሥርዓተ አምልኮት ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ወይም መንፈሳዊ ውሕደት እንደማይቻል ሁሉ ያለ ሐዋርያዊ ክህነት ደግሞ ትክክለኛ አምልኮትን መፈጸም አይቻልም። ይህ ማለት ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ሊኖራቸው የሚችለው መንፈሳዊ ግንኙነትም እንበለው ውሕደት ያለ እውነተኛ ክህነት ሊፈጸም አይችልም ማለት ነው።"

## (የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያው ፓትርያሪክ፣ ቀዳሜ ቃል)

ከላይ የተወሰደው ጽንሰ ሐሳብ ዲያቆን ብርሃኑ አድማስ የመጀመሪያው ፓትርያርክ በተሰኘው መጽሐፍ በቀዳሜ ቃል ላይ ያስቀመጠው መልእክት ነው። እግዚአብሔር አምላካችን በቦታና በጊዜ እንዲሁም በልዩ ልዩ ሁኔታዎች አይወሰንም። ፍጥረታቱን በቀጥታ ለመገናኘትም እርሱን የሚያግደው ነገር የለም። እርሱ እንደወደደና እንደፈቀደ ፈጥሮ በመግቦቱና በአምላካዊ ጥበቃው እየተገናኘም ይኖራል። እርሱ ፈቅዶና ወዶም የሰው ልጅ ከፈጣሪው ጋር የሚገናኝበትን መንገድ እጅግ አብዝቶታል። ከዚህ ከብዙው መገናኛ መንገዱ መካከል ክህነት አንዱ ነው። ይህ የክህነት አገልግሎት ከህገ ልቡና ጀምሮ እስከ አሁን አለ ወደፊትም ይኖራል። ከላይ በዲያቆን ብርሃኑ የተጠቀሰው ጽንሰ ሐሳብ የሚያስረዳን እግዚአብሔር በዚህ የክህነት አገልግሎት አማካኝነት ከሰው ልጆች ጋር ጥብቅ ቁርኝት ሲያደርግ እንደኖረ ወደፊትም እንደሚኖር ነው። ዲያቆን ብርሃኑ በመቀጠልም

"አንዳንድ ሰዎችን የልቡናቸውን ቅንነት አይቶ እግዚአብሔር ቢቀበልላቸው እንኳን ለድኅነት ይበቁ ዘንድ መንገዳቸውን ወደ ትክክለኛው እምነትና ሥርዓተ አምልኮት ይመራቸዋል። ለምሳሌ ያህል ራሱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቆርነሌዎስን ጸሎቱን፣ ምጽዋቱንና የልቡን ቅንነት አይቶ ተቀብሎ ጠርቶታል። ቅዱስ ጳውሎስን ደግሞ ቀናዒነቱንና ለአመነበት ነገር ራሱን አሳልፎ መስጠቱን አይቶ ጠርቶታል። ሁለቱንም በተአምራት ከመለሳቸው በኋላ መጀመሪያ ያደረገው ግን ከካህናት ጋር ማገናኘትና ከቤተ ክርስቲያን ሊያገኙት የሚገባቸውን እንዲያገኙ ማስቻል ነው። መልሶ ከራሱ ያዋሐዳቸው በዚህ ሐዋርያዊ መንገድ ነው።" (ዝኒ ከማሁ) በማለት ያስረዳል።

ይህ ሁሉ የሚያስረዳን የክህነት አገልግሎት ለእውነተኛው ድኅነት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነና ቤተ ክርስቲያን አምልታና አስፍታ የምታስተምረው፣ ምእመናንንም ከእግዚአብሔር ጋር የምታገናኝበት መንገድ መሆኑን ነው። በተለይም በዘመናችን ያለው ትልቁ ተግዳሮት ለክህነት ያለው አመለካከት ከውስጥም ሆነ ከውጭ እጅግ የተዛባ መሆኑ ነው። ከውስጥ ያለው ተግዳሮት

ክህነትን እንደሚገባ ባለመያዝ ከውጭ ያለው ደግሞ ከነአካቴውም አያስፈልግም በማለት የሚሰነዘረው ጦር እጅክ የከፋ መሆኑ ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በአካል ያገኛቸውንና የፈወሳቸውን በሽተኞች ሳይቀር ወደካህን መላኩ የክህነትን አስፈላጊነት በአጽንኦት የሚያስረዳን ነው።

ቤተ ክርስቲያን ከነቢያትና ከሐዋርያት የተለየ አስተምሮም፣ አካሄድም የሥርዓተ አምልኮ አፈጻጸምም የላትም። ምክንያቱም በክርስቶስ ማዕዘንነት በነቢያትና በሐዋርያት መሠረት ላይ ተመሥርታለችና። መጽሐፍ ቅዱስ "በነቢያትና በሐዋርያት መሠረት ላይ ታንጻችኋልና፤ የሕንጻው የማዕዘን ራስ ድንጋይም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱም ሕንጻ ሁሉ የሚያያዝበት የእግዚአብሔርም ቤተ መቅደስ ግንብ የሚያድግበት ነው። (ኤፌ.፪፥፳-፳፩) በማለት ያስረዳናል። ስለዚህ ጥንት ከአበው ጀምሮ ከዚያም በነቢያትም ሆነ በሐዋርያት የነበረው የክህነት አገልግሎት ዛሬም ሕያው ሆኖ አለ። እውነተኛውና ትክክለኛው ሥርዓተ አምልኮት ይፈጸም ዘንድም እግዚአብሔር አምላካችን ይህን ስጦታ አድሎናል። በዚህ ጽሑፍ በተከታታይ እትሞቻችን ከምንነቱ በመነሣት በዘመናት የነበረውን ህልውና በተለይም በዘመናችን ያለበትን ተግዳሮትና በተወሰነ መልኩ የመፍትሄ አቅጣጫም ለመጠቆም እንሞክራለን።

## ፩. የክህነት ምንነት

**ክህነት፡-** ተክህነ ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጓሜውም አገለገለ፣ ተሾመ፣ ዲቁና፣ ቅስና ተቀበለ፣ መንፈሳዊ ሥልጣን ተቀበለ ማለት ነው።

"ተክህነ፤ ተካነ፤ ክህነት ተሾመ፣ ተቀበለ፣ ካህን ሆነ፣ ካህን ተባለ ለማገልገል።ክሂን ከሹመት በኋላ ማገልገልን፣ ተክህኖ ከማገልገል በፊት መሾምን፣ የሹመትን ጊዜ የተቀበሉበትን ዕለትና ሰዓት ያሳያል። ክህነት፤ መካን፣ ማስካን፣ ካህንነት፣ ተክኖ ማገልገል፣ አገልግሎት፣ መንፈሳዊ ሹመት" (ኪዳነ ወልድ፣ገጽ ፫፻፳፪)

ከላይ የተወሰደው ሐሳብ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ በመዝገበ ቃላቸው የሰጡት ትርጉም ነው። ጠቅለል ሲደረግ ክህነት አገልግሎት ሲሆን ይህን አገልግሎት የሚሰጠው አካል ደግሞ ካህን ይባላል። ከዚህ በተጨማሪ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት "ካህን፤ ክህነት፡- በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ሆኖ ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኝ ካህን ይባላል። አገልግሎቱ መሥዋዕትን በመሠዋትና ጸሎትን በመጸለይ ይፈጸማል (የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ ገጽ ፩፻፺፪) በማለት አገልግሎቱ ውስጥ ሊኖር የሚችለውን ጉዳይ በሚያመላክት አገላለጽ ያስረዳል።

ከሁሉቱም አገላለጽ እንደምንረዳው ክህነት አገልግሎቱ ሲሆን ካህን ደግሞ አገልጋዩን የሚወክል ነው። አገልግሎቱም ሆነ አገልጋዩ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለ ግንኙነት ሲሆን ይህን በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለውን አገልግሎት የሚፈጽመው አካል ካህን ሲባል አገልግሎቱ ደግሞ ክህነት ይባላል ማለት ነው። ይህ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የሚከናወን አገልግሎት በልዩ ልዩ አገላለጽ ሊገለጽ ይችላል። የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል ክህነት፡-

### ሀ. መለኮታዊ ጥሪ (ሰማያዊ ምርጫ) ነው።

ክህነት መንፈሳዊ አገልግሎት ነው። መንፈሳዊ አገልግሎት እንደመሆኑ መጠን ደግሞ አምላካዊ ምርጫ ሊኖር ያስፈልጋል። እኛ ስለፈለግን ብቻ

ካህን መሆን አንችልም፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት "እኔ መርጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም" (ዮሐ.፲፭፥፲፮) በማለት ያስተማራቸው ይህን ያስረዳናል፡፡ ስለዚህ ይህ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የሚከናወን መንፈሳዊ አገልግሎት መለኮታዊ ምርጫ ነው፡፡

እዚህ ላይ ምርጫ አለ ሲባል ለአገልግሎት እንጂ ለመንግሥተ ሰማያት ወይም ለገሃነመ እሳት እንዳልሆነ ልብ ልንለው የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ ይህንም በነቢዩ በኤርምያስ ሕይወት መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ‹‹የእግዚአብሔርም ቃል ወደእኔ እንዲህ ሲል መጣ፡ - ‹በእናትህ ሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ፤ ከማኅፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ ለአሕዛብም ነቢይ አድርጌሃለሁ፡፡››› (ኤር.፩፥፭) በማለት እግዚአብሔር ኤርምያስን ለነቢይነት እንደመረጠውና እንደለየው እንረዳለን፡፡ መመረጡ ለአገልግሎት ማለትም በአሕዛብ ዘንድ ነቢይ ሆኖ እስራኤልን እንዲመራ እግዚአብሔርን እንዲያገለግል ነው፡፡ እንደዚሁ ሁሉም ክህነትም አምላካዊ ምርጫ ነው፡፡

ብርሃነ ዓለም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የክህነትን መለኮታዊ ጥሪ መሆን በተመለከተ "እንደ አሮንም በእግዚአብሔር ከተጠራ በቀር ማንም ለራሱ ክብርን የሚወስድ የለም" (ዕብ.፭፥፬) በማለት ከብሉይ ኪዳን ምሳሌውን ጠቅሶ ይህ አምላካዊ ጥሪ ደግሞ ዘለዓለማዊ እንደሆነ ማንም እግዚአብሔር ለዚህ አገልግሎት ሳይጠራው በራሱ ካህን መሆን እችላለሁ ማለት እንደማይችል ያስረዳናል፡፡ በቅዱስ ወንጌልም "ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ ያወጡአቸው ዘንድ ደዌንና ሕማምንም ሁሉ ይፈውሱ ዘንድ በርኵሳን መናፍስት ላይ ሥልጣንን ሰጣቸው" (ማቴ.፲፥፩) ተብሎ ተጽፏል፡፡

## ለ. ክህነት ለሰማያዊ አገልግሎት መለየት ነው

መለየት ነው ሲባል በአካል ተለይቶ ከሕዝቡ ይወጣል ማለት አይደለም፡፡ አገልግሎቱ መንፈሳዊና ሰማያዊውን መንግሥት የሚያስገኝ እንደመሆኑ መጠን ለዚህ ለመንፈሳዊና ሰማያዊ አገልግሎት ከሌላው ማኅበረ ሰብ በተለየ አምላካዊ ሥልጣን ተሰጥቶት ለተቀደሰ አገልግሎት ተወስኖ መኖርን የሚያመለክት ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ "የእግዚአብሔርን ሥራ ሲሠሩ ሲጾሙም መንፈስ ቅዱስ፡- በርናባስንና ሳውልን እኔ ለፈለግኋቸው ሥራ ለዩልኝ አላቸው" (ሐዋ.፲፫፥፪-፫) ተብሎ ተጽፎ እናገኛለን፡፡ ይህ የሚያስረዳን በራሱ በመንፈስ ቅዱስ ለተጠሩለት ሠራ ለሰማያዊው አገልግሎት ማለት በምድር እያሉ ግን ሰማያዊውን ርስት ለሚወርሱበትና ሌላውንም ለሚያወርሱበት አገልግሎት መለየታችውን የሚያመለክት ነው፡፡

**አገልግሎቱ መንፈሳዊና ሰማያዊውን መንግሥት የሚያስገኝ እንደመሆኑ መጠን ለዚህ ለመንፈሳዊና ሰማያዊ አገልግሎት ከሌላው ማኅበረ ሰብ በተለየ አምላካዊ ሥልጣን ተሰጥቶት ለተቀደሰ አገልግሎት ተወስኖ መኖርን የሚያመለክት ነው፡፡**

## ሐ. ክህነት ታማኝ መጋቢነት ነው

ካህኑ የመንጋዎች መጋቢ ነው:: የሚመግበው ደግሞ ሰማያዊውን ምግብ ነው:: በቅዱስ ወንጌል "ምግባቸውን በየጊዜው ይሰጣቸው ዘንድ ጌታው በቤተሰቡ ላይ የሚሾመው ደግ ታማኝና ብልህ መጋቢ ማን ይሆን? ጌታው በመጣ ጊዜ እንዲህ ሲያደርግ ያገኘው አገልጋይ ብፁዕ ነው" (ሉቃ.፲፪፥፵፪) ተብሎ እንደተጻፈ ክህነት የሚባለውም ይህን የተቀደሰ አገልግሎት አምኖና የሚያስከፍለውንም ዋጋ ተረድቶ መግባት ነው:: ክብር ያለበት መከራም በዚያው ልክ አለበትና:: መንጋውን ለመመገብ ሲባል መጋቢው ራሱ ሊራብ ይችላል:: መንጋውን ሰማያዊ ምግብ ሊመግብ ሲተጋ እርሱ ደግሞ በምድራዊው ምግብ መራቡ አይቀርምና ይህን ሁሉ ጫና መቀበል ታማኝ አገልግሎት ያስብላል:: ይህን አደራ ለተወጣው ደግሞ ታማኝ ከመባል በላይ ብፁዕ ያስብላል::

# ፪. ክህነት በዘመናት

ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ "ኢኃደጋ ለምድር እምቅድመ ዓለም ወእስከ ለዓለም እንበለ ካህናት ወዲያቆናት ዘካርያስ ካህን፣ ነቢይ ወሰማዕት ዘርእየ ተቅዋመ ማኅቶት፤ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት እስከ ዘለዓለም ድረስ ምድርን ያለ ካህናትና ዲያቆናት አልተዋትም፤ ካህን፣ ነቢይና ሰማዕት የተባለ ዘካርያስ የብርሃን መቅረዝን አየ" (ዚቅ ዘህዳር ጽዮን) በማለት እንደገለጸው የክህነት አገልግሎት ከሰው ልጅ መፈጠር ጀምሮ የነበረ ዛሬም ያለ ወደፊትም የሚቀጥል ነው:: የነበረበት ሁኔታና ራሱ ክህነቱ የሚገኝበት መንገድ ግን እንደየዘመናቱ የተለያየ ነበር:: በተወሰነ መልኩ እንደሚከተለው ለማየት እንሞክራለን::

## ሀ. በብሉይ ኪዳን

የመጀመሪያው ካህን አዳም ነው:: ከሰማንያ አሐዱ ቅዱሳት መጻሕፍት አንዱ በሆነው በመጽሐፈ ቀሌምንጦስ "ወእምዝ አልበሶ እግዚአብሔር ለአቡነ አዳም ልብሰ መንግሥት ወአክሊለ ስብሐት ወዕበየ ግርማ ወክብር ዲበ ርእሱ ወአስተቀጸሎ አክሊለ መንግሥት ወበህየ ረሰዮ ንጉሠ ወካህነ ወነቢየ ወአንበሮ እግዚአብሔር ዲበ መንበረ ክብር፤ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔር አባታችን አዳምን የምስጋና አክሊን፣ ልብሰ መንግሥትን፣ የግርማ ከፍተኛነትን፣አለበሰው በራሱ ላይም የመንግሥትን አክሊል አቀዳጀው:: በዚህ ጊዜ ንጉሥነትን፣ ክህነትን፣ ነቢይነትን ሰጠው በክብር መንበር ላይም አስቀመጠው:: (መጽሐፈ ቀሌምንጦስ ፩፥፵) የሚል ክፍል ምንባብ እናገኛለን:: በዚሁ መጽሐፍ "ወእምዝ ሰምዑ መላእክት ቃለ እግዚአብሔር ልዑል እንዘ ይብል ኦ አዳም ናሁ ረሰይኩከ ንጉሠ ወካህነ ነቢየ ወመስፍነ ወመኰንነ ኵሉ ፍጥረት፤ በዚህም ጊዜ መላእክት የእግዚአብሔር ቃል አዳም ሆይ እነሆ ካህን፣ ንጉሥ፣ ነቢይ መስፍን ለፍጥረት ሁሉ ገዥ አደረግሁህ ሲል ሰሙ::" (ቀሌምንጦስ ፩፥፵፫) ተብሎም ተጽፎ እናገኛለን::

ይህ ከላይ የተጠቀሰው ክፍለ ምንባብ የሚያስረዳን እግዚአብሔር አምላካችን ለአባታችን ለአዳም ከአደለው በርካታ ጸጋዎች መካከል አንዱ ክህነት መሆኑን እና የመጀመሪያው ካህንም አባታችን አዳም እንደሆነ ነው:: የአዳምን ካህንነትና የክህነት አገልግሎት ይፈጽም እንደነበረም በመጽሐፍ ቅዱስ "በዚችም ቀን አዳም ከኤዶም ገነት ሲወጣ ለበጎ መዓዛ ነጭ ዕጣን፣ ቀንዓትና ልባንጃ ስንቡልም ኀፍረቱን በሸፈነበት ቀን በጥዋት ፀሐይ ሲወጣ ዐጠነ" (ኩፋ.፫፥፩) ተብሎ ተመዝግቦ እናገኛለን:: ይህን የክህነት አገልግሎት ማለትም መሥዋዕት የመሠዋት አገልግሎትን በግለሰብም ሆነ በቤተሰብ ደረጃ ያከናወኑ የነበሩት አበው ቢሆንም በመጽሐፍ ቅዱስ የልዑል እግዚአብሔር ካህን ተብሎ ተመዝግቦ የምናገኘው ካህኑን መልከ ጼዴቅን ነው::

# መልከጼዴቅ

ከአዳም ቀጥሎ በመጽሐፍ ቅዱስ ካህን የተባለ መልከ ጼዴቅ ነው። ለማሳያ ያህል የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እንመልከት። "የሳሌም ንጉሥ መልከ ጼዴቅም እንጀራንና የወይን ጠጅ አወጣ፤ እርሱም የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበረ። አብራምንም ባረከው፤ አብራም ሰማይንና ምድርን ለፈጠረ ለልዑል እግዚአብሔር የተባረከ ነው፤ጠላቶችህን በእጅህ የጣለልህ ልዑል እግዚአብሔር ቡሩክ ነው አለው። አብራምም ከሁሉ ዐሥራትን ሰጠው" (ዘፍ.፲፬፥፲፰-፳)

ነቢዩ ዳዊት "እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት አንተ ለዘለዓለም ካህን ነህ ብሎ እግዚአብሔር ማለ አይጸጸትም" (መዝ.፻፱፥፬) በማለት ስለጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተናገረው ትንቢት አስረድቷል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ ለዕብራውያን በላከላቸው መልእክቱ "የሳሌም ንጉሥ የልዑል እግዚአብሔርም ካህን የሆነ ይህ መልከ ጼዴቅ አብርሃም ነገሥታትን ደል ነሥቶ በተመለሰ ጊዜ ከእርሱ ጋር ተገናኝቶ ባረከው። አብርሃምም ከገንዘቡ ሁሉ ከዐሥር አንድ ሰጠው፤መጀመሪያ የስሙ ትርጓሜ የጽድቅ ንጉሥ ነበር፤ በኋላም የሳሌም ንጉሥ ተባለ፤ የሰላም ንጉሥ ማለት ነው።…ክህነቱ የወልደ እግዚአብሔር ምሳሌ ሆኖ ለዘለዓለም ይኖራል" (ዕብ.፯፥፩-፫)

የመልከ ጼዴቅ ክህነት ከላይ በተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የልዑል እግዚአብሔር ካህን እንደሆነ፣ በራሱ በእግዚአብሔር የተሾመ መሆኑን የሊቀ ካህናት የኢየሱስ ክርስቶስ ክህነት ምሳሌ ተብሎ ተገልጾ እናገኘዋለን። ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ በሊቁ በቅዱስ ያሬድ "አክሊለ ሰማዕት ሰያሜ ካህናት፤ የሰማዕታት አክሊል የካህናት ሿሚ" ተብሎ የሚነገርለት ማንም የሚሾመው የሌለው ሹመቱ የባሕርዩ የሆነ የካህናት አለቃ ነው። ካህኑ መልከ ጼዴቅም በሰው እጅ ስላልተሾመ የክስርቶስ ምሳሌ ሁኖ ይጠቀሳል።

በሕገ ኦሪትም እግዚአብሔር ሕግን ሠርቶ ለሙሴ ከሰጠው በኋላ አሮንን መርጦ በክህነት አገልግሎት እንዲኖር እንዲሁ ከሌዊ ዘር የተወለደ ሁሉ በዚህ ክህነት ገልግሎት እንዲኖርና እግዚአብሔርን እንዲገለግሉ በሙሴ አማካኝነት ሥርዓት ሠርቶ ሕዝቡ በዚህ አገልግሎት ሲጠቀሙ ኖረዋል።

**የሐዲስ ኪዳን ክህነት እንደ ኦሪቱ በዘር፣ በቤተ ሰብ የሚወረስ ሳይሆን ርትዕት በሆነችው ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖት ያለና የሚገባውን ትምህርት የተማረ እንዲሁ እግዚአብሔር ለዚህ አገልግሎት የመረጠው ሁሉ የሚሾመው ሹመት ነው።**

## ለ. በሐዲስ ኪዳን

ክህነት፡-በዕለተ ዕርገቱ ለሰው ልጆች ከሰጣቸው ስጦታዎች አንዱ የሐዲስ ኪዳኑ የክህነት አገልግሎት ነው። "ወእምዝ አውጽኦሙ አፍኣ እስከ ቢታንያ ወአንሥአ እደዊሁ ወአንበረ ላሌሆሙ ወባረኮሙ። ወእንዘ ይባርኮሙ ተረኀቆሙ ወዐርገ ሰማየ፤ እስከ ቢታንያም ወደ ውጭ አወጣቸው፤ እጁንም አንሥቶ በላያቸውም ጭኖ ባረካቸው።እየባረካቸውም ራቃቸው፤ ወደ ሰማይም ዐረገ።›› (ሉቃ.፳፬፥፶-፶፩) በማለት ቅዱስ ሉቃስ እንደጻፈልን ዛሬ ያለውን የክህነት ደረጃ ከአጻዌ ኆኅት ጀምሮ እስከፓትርያርክ ድረስ በአንብሮተ እድ (እጅን በመጫን) ሾሟቸው ዐረገ።

ይህ የሐዲስ ኪዳን ክህነት እንደ ኦሪቱ በዘር፣ በቤተ ሰብ የሚወረስ ሳይሆን ርትዕት በሆነችው ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖት ያለና የሚገባውን ትምህርት የተማረ እንዲሁ እግዚአብሔር ለዚህ

አገልግሎት የመረጠው ሁሉ የሚሾመው ሹመት ነው፡፡ የኦሪቱ ክህነት አማናዊ ሥርየትን አያስገኝም የሐዲስ ኪዳኑ ክህነት ግን "የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻ እሰጥሃለሁ፤ በምድር የምታስረው በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድርም የምትፈታው በሰማይም የተፈታ ይሆናል" በማለት እውነተኛውን ክህነት ማሰር መፍታት የሚያስችለውን ክህነት ሰጣቸው፡፡

እዚህ ላይ አንድ ልብ ልንለው የሚገባን ነገር ቢኖር መምህረ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ሀብተ ክህነትን ከሰጣቸው በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ባልጸና ሰውነታቸው ቢፈተኑ እንደማይጸኑ ያውቃልና አንድ ትዝዛዝ አዘዛቸው ትእዛዙም እንዲህ የሚል ነበር፡፡ "እነሆም አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ፤ እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ፡፡›› (ሉቃ.፳፬፥፵፱)

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ለዐርባ ቀን ያህል ኪዳንንና ትምህር ኅቡዓትን ሲያስትምራቸው ከቆየ በኋላ በዓርባኛው ቀን ወደ ሰማይ ዐረገ፡፡ ወደ ሰማይ ሲያርግ ከላይ እንደጠቀስነው ለሰው ልጅ ሁሉ የሚያስፈልጋቸውን ጸጋ ሰጠ፤ ደቀ መዛሙርቱን ደግሞ በኢየሩሳሌም ቆዩ ብሏቸው ዐረገ፡፡ ኢየሩሳሌም ማለት የሰላም ሀገር የሰላም ከተማ ማለት ነው፡፡ ዛሬም እነተኞች ካህናት ሰላም ከሰፈነባት ሰላም ከማይለይባት የሰላም ከተማ ከሆነችው ቤተ ክርስቲያን፣ ጉባኤ ቤት፣ ገዳም ይገኛሉ፡፡ ስለዚህ ከፈተና የሚያጸኑንንና አስቀድሞ የተሰጡትን ጸጋዎች ከእኛ እንዳይነጠቁን ለማድረግ የሰላም ከተማ ከተባሉት ቤተ ክርስቲያን ቤተ ጉባኤ እና ከገዳም መለየት የለብንም፡፡ ይህ ሲባልም ሁሉ ገዳም ይግባ ማለት እንዳልሆነ ልብ ልንለው ይገባል፡፡ በገዳም ያለ ከገዳሙ፣ ጉባኤ ቤት ያለ ከጉባኤ ቤቱ እንዲሁም በአርባ በሰማንያ ቀን ከሥላሴ ተወልዶ ሀብተ ወልድና ስመ ክርስትና የተቀበለ ሁሉ ከቤተ ክርስቲያን መለየት የለበትም ሲለን ነው

## ሐ. በሊቃውንት

ክህነት በሐዲስ ኪዳን አማናዊ ሥርየተ ኃጢያትን የሚያሰጥና ሰማያዊ የሆነ አገልግሎት ነው፡፡ ይህን የሐዲስ ኪዳን ክህነት ከሐዋርያት ጀምሮ በሊቃውንትም ዘንድ ሳይቋረጥ እስከ አሁን ደርሷል፡፡ እንዳልተቋረጠ የሚያረጋግጥልን ሊቁ ቅዱስ አትናቴዎስ በቅዳሴው ‹‹ኦ ካህናት አንትሙ ውእቱ አእይንተ እግዚአብሔር ብሩሃት፤ እናንተ ካህናት ሆይ የእግዚአብሔር ዐይኖች ናችሁና ኃጢአተኛውን እንደወንድማችሁ ገሥጹት፡፡" በማለት በቅዳሴው ገልጾት እናገኛለን፡፡ ይህም መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው አንትሙ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም፤ እናንተ ያለም ብርሃን ናችሁ በማለት የሰጣቸውን ክህነት እንዳይዘነጉ በማስታዎስ ያላቸውን ልዕልና ያስረዳል፡፡

ክህነቱ ቢቋረጠጥ የሌለን አገልግሎት አድርጉ እያለ ኃላፊነታቸውን ባላስረዳ ነበር፡፡ እንዲሁ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት "እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ከእናንተ ጋር ነኝ" (ማቴ.፳፰፥፳) በማለት ያስረዳቸው በእነርሱ እግር ተተክተው የሚያገለግሉትን ሁሉ እንጂ ሐዋርያት በአጸደ ሥጋ እስከ ዓለም ፍጻሜ ይኖራሉ ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡ ሊቁ አባ ሕርያቆስም "ኦ አንትሙ አበዊነ ንቡራነ እድ ሥዩማን እለ መትልወ ሐዋርያት እስመ ነሣእናክሙ አስተብቋዕያነ ለነ ለኀበ እግዚአብሔር፤ የሐዋርያት ተከታዮች የሆናችሁ በአንብሮተ እድ (እጅ በመጫን) የተሾማችሁ አባቶች ሆይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእኛ የምታማልዱ እናንተን ተቀብለናችኋል እኮን" በማለት ያስረዳው ክህነቱ ያላቋረጠ መሆኑን ሲያስረዳን ነው፡፡

እንግዲህ ይህ አገልግሎት በምድር ያለ ግን ሰማያዊ ክብርን የሚያሰጥ፣ በምድር ለሰማያዊ ክብርና ጸጋ የሚወጡበት የሚወርዱበት ነው፡፡ አገልግሎቱም አገልጋዮችም ከእግዚአብሔር የተሰጡ እንደሆኑም ሊቁ ያስረዳል፡፡ በዚህ እትም ምንነቱንና በዘመናት የነበረ ወደፊትም የሚኖር መሆኑን ከተመለከትን ቀሪ ጉዳዮችን ደግሞ በሚቀጥለው እንመለከታለን፡፡ ይቀጥላል…

# “መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ”።

(ዕብ.፲፫፥፲፮)

## ክርስትና በማኅበራዊ ሕይወት

*በተስፋዬ ምትኩ*

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያንመልእክቱ በክርስቶስ ክርስቲያን በወልድ ውሉደ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ መንፈሳውያን የተሰኙ ምእመናን ሕይወታቸው (አኗኗራቸው) ምን መምሰል እንዳለበት ሲናገር “መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ፤ እንዲህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና” ብሏል።(ዕብ.፲፫፥፲፮)ለመሆኑ መልካም የተባለው ምንድን ነው?መልካም ማድረግና ለሌሎች ማካፈልስ እንዴት ነው? የሚለው በዚህ ጽሑፍ በስፋት የምንመለከተው ርእሰ ጉዳያችንነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሕይወቱ መምህሩን ክርስቶስን የመሰለ እና ለምእመናንም እኔን ምሰሉ ብሎ ለመናገር የበቃ ታላቅ መምህር ነው። “እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ” እንዲል። (፩ኛቆሮ.፲፩፥፩) እንደሚታወቀው ክርስቲያን የሚለውየክርስቶስ ወገን ወይም የክርስቶስ ደቀ መዝሙር ማለት ነው። አንድ ተማሪ “የእገሌ ደቀመዝሙር ነው” የሚባለው በሕይወቱ መምህሩን መምሰል ሲችል ብቻ ነው። አለበለዚያ ግን “እኔ የእገሌ ደቀመዝሙር ነኝ” ስላለ ብቻ ደቀ መዝሙርነቱ ተቀባይነት ሊያገኝ አይችልም። የክርስቶስ ደቀ መዝሙርነቱም ሊገለጥ የሚችለው ክርስቶስ የሠራውን ሥራ በመሥራት ነው። ክርስቶስ በዚህ ምድር የሠራው ሁሉ ለእኛ መልካም ምሳሌ ለመሆን ነውና እኛም ክርስቲያን ተብለን በስሙ እስከተጠራን ድረስ በስም ብቻ ሳይሆን በአኗኗራችንም እርሱ የተናገረውንና ያከናወነውን መልካም ነገር ሁሉ በተግባር በመፈጸም ልንመስለው ይገባናል።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው ሲያስተምር አንድ ሰው ወደ እርሱ ቀርቦ “መምህር ሆይ፥ የዘለዓለምን ሕይወት እንዳገኝ ምን መልካም ነገር ላድርግ?” ብሎ ጠይቆ ነበር። ጌታም “ስለ መልካም ነገር ለምን ትጠይቀኛለህ? መልካም የሆነ አንድ ነው፤ ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ግን ትእዛዛትን ጠብቅ” ሲል መልሶለታል። ይህ ሰው ጥያቄውን በዚያ አላቆመም “የትኞቹን” ሲል ደግሞ ጠየቀው። ጌታም “አትግደል፥ አታመንዝር፥ አትስረቅ፥ በሐሰት አትመስክር፥ አባትህንና እናትህን አክብር፥ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ” በማለት ዐሠርቱ ሕግጋተ ኦሪትን ዘርዝሮለታል። (ማቴ.፲፱፥፲፮-፲፱)

እዚህ ላይ “መልካም የሆነው አንድ ነው፤” የሚለውና “ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ትእዛዛቱን ጠብቅ” የሚሉት ሐሳቦች መልካም የተባለው ሕገ እግዚአብሔር መሆኑንና መልካም ማድረግ የተባለውምይህን ሕገ እግዚአብሔርን መፈጸም መሆኑን ያስገነዝቡናል። እግዚአብሔር በባሕርዩ መልካም ነው። ከመልካምነት ውጭእግዚአብሔርን ማሰብም ሆነ ማወቅ አንችልም። ሐሳቡም ሥራውም፣ አጠቃላይ ባሕርዩም መልካምነት ነው። ሕግጋቱና ትእዛዛቱም መልካም ናቸው። መልካምነትን ገንዘብ ያደረጉ ሰዎች ደግሞ ሕግጋቱን ይጠብቃሉ፤ ትእዛዛቱንም እየፈጸሙ እንደፈቃዱ ይመላለሳሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን “እንዲህ ነው፣ እንዲያ ነው” እያለ ማንነቱን ከገለጠባቸው መገለጫዎችመካከል“እግዚአብሔር ቅዱስ ነው”፤ “እግዚአብሔር ፍቅር ነው”፤ “እግዚአብሔር እውነተኛ ዳኛ ነው”፤ “እግዚአብሔር ቸር እረኛ ነው” ፤ “እግዚአብሔር መሐሪ ነው፤ ኤልሻዳይ፣ ሁሉን ቻይ አምላክ ነው” ወዘተ የሚሉትን ኃይለቃላት

እናገኛቸዋለን፡፡ “እግዚአብሔር መልካም ነው” የሚለው የእግዚአብሔርን ባሕርይ ገላጭ ከሆኑት አንዱ ነው፡፡ “እግዚአብሔር መልካም ነው በመከራ ቀንምመሸሸጊያ ነው” እንዲል፡፡ (ናሆ.፩፥፯)

ይኸውም “መልካምነት” ከእግዚአብሔር የባሕርይ መገለጫዎች አንዱ መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡ ይሁን እንጂ መልካምነት ሁሉ እግዚአብሔር ነው ወይም ከእግዚአብሔር ነው ማለት አይቻለም፡፡ ሰዎች ለመልካምነት ያላቸው ግንዛቤ ይለያያልና፡፡ ለአንዱ መልካም የሆነም ለሌላ ክፉ ሊሆን ይችላል፡፡ እንደ ክርስትና አስተምህሮ ደግም ከእግዚአብሔር የሆነ ሁሉ መልካም ነው፡፡ መከራና ሥቃይ፣ ሕመምና ሞት፣ ኀዘንና ጭንቀት እንኳን ቢሆኑ ከእግዚአብሔር የሆኑ እንደሆነ መልካም ነው፡፡ ምን አልባት መልካምነታቸው ምን ላይ እንደሆነ ሰዎች ለጊዜው ተመራምረው ላይደርሱበት ይችሉ ይሆናል እንጂ እግዚአብሔር ለፍጥረቱ መልካምን እንጂ ክፉ የሆነውን አያስብም አያደርግምም፡፡ “ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም” እንዲል፡፡ (ኤር.፳፱፥፲፩)

ስለ መልካምነት ይህን ካልን መልካምነትን ለሌሎች ስለማካፈል እንመልከት፡፡ ክርስቲያናዊ ሕይወት የመካፈል ሕይወት ነው፡፡ ምክንያቱም ክርስትና፡-

እግዚአብሔር ሰውንበመልኩናበምሳሌውእንደፈጠረው፣ ልጅነትንና ርስትን እንደሰጠው፣ ከእርሱ በታች ሆኖ ፍጥረታትን ሁሉ ይገዛ ዘንድ የእርሱ ብቻ የሆነውን ሥልጣን እንዳደለው ማመን ነውና፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አዳም ከክብር በተዋረደ ጊዜ አንድያ ልጁን ልኮ በልጁ ሞት እንዳዳነው የባሕርይ ልጁ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ሥጋውን ቆርሶ ደሙንም አፍስሶ ምግበ ነፍስ አድርጎ እንደሰጠን በልተንና ጠጥተን የስሙ ቀዳሾች የመንግሥቱ ወራሶችእንድንሆን ማድረጉን ማመን ነው፡፡ ታዲያ የምናመልከው ጌታ አንዳች ነገር ላናደርግለት በቸርነቱ ፈጥሮን፣ ምንም ሳይሰስት የክብሩወራሾች እስከመሆን ድረስ የእርሱ የሆነውን ሁሉ ከሰጠን፣ ከእርሱ ከተቀበልነው ውጭ የእኛ የሆነ አንዳች ነገር እንደሌሌንም ካመንን፣ እኛም ያለንን ለሌሎች ልናካፍል ይጋባል፡፡

ያለንን ማካፈል ስንል ብዙ ጊዜ ትዝ የሚለን፣ የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ ላጡትና ለተቸገሩት ሰዎች ቆርሶ ማጉረስን ቀዶ ማልበስን ነው፡፡ ይህ ተገቢና አስፋላጊ ነው፡፡ ጌታም ይህንኑ እንድናደርግ አስተምሮናል፡፡ ለፍርድ በሚመጣበትም ጊዜ ጻድቃንን “የአባቴ ብሩካን ወደ እኔ ኑ” ብሎ የሚፈርድላቸው፣ኃጥአንን ደግሞ “ከእኔ ሂዱ፤ ወግዱ” ብሎ የሚፈርድባቸው በአጠገባቸው ያሉትን ድሆች መርዳታቸውንና አለመርዳታቸውን ወይም ትእዛዛቱን መፈጸምና አለመፈጸማቸውን መሠረት አድርጎ ነው፡፡ ይህን ስንል ግን የምንጸድቅበትና የምንኰነንበት ዋናውና ብቸኛ ምክንያት ይህ ነው ማለት አይደለም፡፡ ዋናው ሃይማኖት ነው፤ ከሃይማኖት ምግባር ይከተላል፤ ፍቅረ እግዚአብሔርና ፍቅረ ቢጽ፣ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም መኖርም ሰውን ወደ ጽድቅ ከሚመሩ ነገሮች ዋነኞቹ ናቸው፡፡ ማካፈልም የሚገባን በዋናነት እነዚህን ነው፡፡ የመንፈሳዊነት መሠረቱ እነዚህ ናቸውና፡፡

## ሀ. ሃይማኖትን ማካፈል፡-

ሃይማኖት መሠረት ነው፡፡ ምግባር ትሩፋት ደግሞ ግድግዳና ጣሪያ ናቸው፡፡ ቤት መሠራት የሚጀምረው ከመሠረት ነው፡፡ መሠረት ሳይኖር ግድግዳና ጣሪያ መሥራት አይቻልምና፡፡ ቢሠራ እንኳ ዋጋ የለውም፡፡ ምክንያቱም ንፋስ ቢነፍስ አሊያም ጎርፍ ቢመጣ ያፈርሰዋልና፡፡ (ማቴ.፯፥፳፯) ለዚህ ነው ቤተ ክርስቲያናችን ምግባር ትሩፋት መሥራትን ከማስተማሯ በፊት ሃይማኖትን የምታስተምረው፡፡ መሠረት የሌለው ቤት አይቆምም፡፡ ሃይማኖት ሳይኖረን መልካም ሥራ መሥራትም ብቻውን ሰማያዊ ዋጋ ሊያሰጠን አይችልም፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም

ይህን አስመልክቶ "ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሰው አስቀድሞ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚሹትም ዋጋ እንደሚሰጣቸውሊያምን ይገባዋል" በማለት የእግዚአብሔርን ቃል ያስተምራል። (ዕብ.፲፩፥፮)

የመልካምነት ምንጩ እግዚአብሔር ነው። ስለሆነም መልካምነትን ገንዘባችን ለማድረግ መልካምነት የባሕርይ ገንዘቡ ከሆነው ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት ሊኖረን ይገባል። የእግዚአብሔር ልጆችና ወዳጆች የምንሆንበት ምሥጢር ደግሞ ሃይማኖት ነው። እግዚአብሔር የሁሉ ፈጣሪ ቢሆንም አባትነቱ ግን ወደው ፈቅደው ለተቀበሉት ብቻ ነውና። "ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤" እንዲል። (ዮሐ.፩፥፲፪) ስለሆነም ሀልወተ እግዚአብሔርን አምነን፣ በስመ ሥላሴ ተጠምቀን፣ በወልድ ውሉደ እግዚአብሔር ለመሆን የታደልን እኛ ምእመናን ይህን ዕድል ያላገኙትን ወገኖች ከእኛ ጋር አንድ እንዲሆኑ የክርስትናን ምንነትናየክርስቶስን ማንነት፣ የእግዚአብሔር ልጅ የመሆንን ምሥጢር ልናስተምራቸው (ልናካፍላቸው) ይገባል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለመዳን እግዚአብሔርን ማመንና ስሙን እየጠሩ ማምለክ፣ እንደሚገባ ባስተማረበት አንቀጽ ዓለም ሁሉ ስሙን ጠርቶ እንዲድን ማስተማር የእኛ የምእመናን ኃላፊነት መሆኑን ሲያስገነዝበን "የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና። እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ?"በማለት ይጠይቀናል። (ሮሜ ፲፥፲፫-፲፬)

እዚህ ላይ ሰባኪ የሚለው ሕይወታቸውን ለዚሁ አገልግሎት የለዩትን ወገኖች ብቻ የሚመለከት አይደለም። እያንዳንዱ ሰው ስለ ሕይወት መንገድ የሰማውን፣ ያነበበውን፣ ሲከናወን ያየውን እውነት ለባልንጀራው የመናገር፣የማካፈል ብሎም የመመስከር ሃይማኖታዊ ግዴታ አለበት።

**የመልካምነት ምንጩ እግዚአብሔር ነው። ስለሆነም መልካምነትን ገንዘባችን ለማድረግ መልካምነት የባሕርይ ገንዘቡ ከሆነው ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት ሊኖረን ይገባል። የእግዚአብሔር ልጆችና ወዳጆች የምንሆንበት ምሥጢር ደግሞ ሃይማኖት ነው።**

## ለ. በጎ አርአያ መሆን፡-

አርአያ መሆን ሲባል በዕለት ተዕለት መንፈሳዊና ማኅበራዊ ሕይወታችን ሁሉ ሰውንና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ መልካም ነገርን በማድረግ በመልካም ሕይወታችን፣ በበጎ ምግባራችን ሌሎችም በጎ ነገር እንዲሠሩ ማድረግ ነው። ይህም በጎነትን ለሌሎች ማካፈል ወይም አርአያ መሆን ነው።በጎ አርአያነት በአንድ ማኅበረሰብ ወይም ተቋም ተቀባይነትን ያገኘ፣ የተወደደ እና የተለመደ ባህልንም ያመለክታል። በማኅበረሰብ ውስጥ እየኖረ ከማኅበረሰቡ ልማድና ሥርዐት ውጭ የሆነ ግለሰብ ቢገኝ ማኅበረሰቡ አንተ እኛን ስለማትወክል ከእኛ ጋር መኖር አትችልም ብሎ ማውገዝ የተለመደ ነው። አልፎ ተርፎም፣ ከምግባሩ ብልሹነት የተነሣ

ይናቃል፤ ይተቻል፤ ይገፋል፤ ይገለላልም፡፡ ምክንያቱም ማንነቱ ኅበረተሰቡን አይወክልምና፡፡ እንደ ክርስትና ግን መልካም ምግባር ስንል ሕግጋተ እግዚአብሔርን ይመለከታል፡፡ እንደ ክርስትናም የበጎምግባር መሠረቱ እግዚአብሔር አታድርጉ ያለውን መተው፣ አድርጉ ያለውንም መፈጸም ነው፡፡

ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ሕግ የማይጻረር እስከሆነ ድርስ የማኅበረሰብን ወግና ልማድንም አብረው ይሳተፋሉ እንጂ አይቃወሙም፡፡ የመሳተፋቸው ዋና ዓላማም የማኅበረሰቡን ልማድ ለመካፈል ብቻ አይደለም፤ አጋጣሚዎችን ተጠቅመው ክርስቲያናዊ ምግባራትን ለማኅበራሰባቸው ለማካፈል ነው እንጂ፡፡ እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ሌሎችን ወደ እውነተኛው የሕይወት መንገድ ለመመለስ ሲሉ ከክርስቲያናዊ ሕይወታቸው የሚጣረስ ሥራ ጭምር እስከ መሥራት የሚያደርስ መሥዋዕትነትን ይከፍላሉ፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን እውነት ሲናገር፡- "እኔ ከሁሉ ይልቅ ነጻ ስሆን ብዙዎችን ወደ ሃይማኖት እሰበስባቸው ዘንድ እንደ ባሪያ ራሴን ለሁሉ አስገዛሁ፡፡ አይሁድን እጠቅማቸው ዘንድ ለአይሁድ እንደ አይሁዳዊ ሆንሁላቸው፤ ከኦሪት በታች ያሉትን እጠቅም ዘንድ፥  ራሴ ከኦሪት በታች ሳልሆን፥ ከኦሪት በታች ላሉት ከኦሪት በታች እንዳለ ሰው ሆንሁላቸው፡፡የእግዚአብሔርን ሕግ የዘነጋሁ ሳልሆን በክርስቶስ ሕግም ሳለሁ፥ ሕግ የሌላቸውን እጠቅም ዘንድ ሕግ ለሌላቸው ሕግ እንደ ሌለው ሆንሁላቸው፡፡ ደካሞችንም እጠቅማቸው ዘንድ ለደካሞች እንደ ደካማ ሆንሁላቸው፤ በሁሉ መንገድ አንዳንዶቹን አድን ዘንድ፥ ከሁሉ ጋር በሁሉ ነገር እንደ እነርሱ ሆንሁ፡፡ በወንጌልም ትምህርት አንድነት ይኖረኝ  ዘንድ ስለ ወንጌል ትምህርት ሁሉን አደርጋለሁ"ብሏል፡፡ (፩ኛ ቆሮ.፱፥፲፱-፳፫)

ሰዎችን ቀርበን ተወዳጅተን፣ እንጂ ርቀን ቆመን በቃላት ጋጋታ ብቻ ወደ ትክክለኛው የእውነት መንገድ መመለስ አንችልም፡፡ ስሕተታቸውን ነቅሰን አውጥተን፣ በመተቸትና በመንቀፍም ቢሆን ተስፋ ከማስቆረጥ በስተቀር አንጠቅማቸውም፡፡ ከዚህ ይልቅ በአካል ቀርበን የችግራቸውን ምንጭ የስሕተታቸውን መነሻ የድካማቸውንም ጥግ መረዳት ይጠበቅብናል፡፡ ለዚህ ደግሞ የእኛ የሆነውን የሕይወት ልምድ ከማካፈላችን በፊት የእነሱንም ድካም መጋራት ካልቻልን መፍትሔ ማምጣት የሚቻል አይደለም፡፡ ይህን ስንል ግን ያለአቅማችን በስሕተት ውስጥ መዘፈቅ ማለት አይደለም፡፡ ጌታ ደቀመዛሙርቱን ወደ ዓለም ሲልካቸው "እንደ እባብ ልባሞች እንደ ርግብም የዋሆች ሁኑ" ያላቸውን ቃል ማስታወስ ይጠበቅብናል፡፡ የሌሎችን የምግባር ጉድለት ለመሙላት ብለን እኛ ሃይማኖታችንን እስከማጣት እንዳንደርስም መጠንቀቅ ይጠበቅብናል፡፡

## ሐ. ሰላምን ማካፈል፡-

ሰላም ከሌሎች ጋር በስምምነትና በአንድነት አብሮ መኖር ማለት ነው፡፡ ሰላም የዕረፍት የደስታ የፀጥታና የርጋታ ስሜት ነው፡፡ ሰላም የሰው ልጅ በዚህ ምድር ለመኖር እጅግ ከሚያስፈልጉት መሠረታዊ ነገሮች አንዱ ነው፡፡ ያለሰላም ወጥቶ መግባት ሠርቶ መብላት የአእምሮ ርካታና የልብ ደስታ ማግኘት አይቻልም፡፡ የሰው ልጅ የዚህን ምድር ኑሮ እንዲሰለች በመንፈሳዊው ሕይወትም ተስፋ እንዲቆርጥ የሚያደርገው ዋነኛው ጉዳይ ሰላምን ማጣቱ ነው፡፡

የሰላም ምንጭ እግዚአብሔር ሲሆን የሰው ልጅ ለሰላም ማጣቱ ምክንያት ደግሞ ዲያብሎስን በግብር መወዳጀት ነው፡፡ አባታችን አዳም በገነት በነበረበት ዘመን በሕይወቱ ፍጹም ሰላም ነበረው፡፡ ያለምንም ጭንቀት በተረጋጋ ሕይወት እግዚአብሔርን እያመሰገነ ይኖር ነበር፡፡ ሰውነቱን የሚሸፍንበት ልብስ ሳይኖረው ጸጋ እግዚአብሔርን ስለለበሰ አይበርደውም ነበር፡፡ የዲያብሎስን ምክር ሰምቶ ከእግዚአብሔር ጋር ሲጣላ ግን ሰላመ እግዚአብሔር ራቀውና ራቁትነቱ ታወቀው፤ ፍርሀት ፍርሀትም ስላለው በገነት ዛፎች መካከል

መሸሸግ ጀመረ። በጥፋቱም ከገነት ተባረረ። ይህ አልበቃ ብሎት በተሰደደባት ምድር ላይ መኖር ሲጀምር ረሀብ፣ እርዛት፣ ጤና ማጣት፣ ግርማ ሌሊት፣ ጸብአ አጋንንት፣ ድምፀ አራዊት ወዘተ ሰላሙን አሳጡት። ከእግዚአብሔር የራቀ ሰው ሰላም አይኖረውምና። የሰላም አምላክ ክርስቶስ መጥቶ "ሰላም ላንተ ይሁን" እስካለበት ቀን እና ሰዓት ድረስ አዳም በሕይወቱ ሰላም አልነበረውም።

ሰላም መሆን ስንል ከሦስት ነገሮች ጋር ነው፤ ማለትም ከራሳችን ጋር፣ ከእግዚአብሔር ጋር እና ከሌሎች ሰዎች ጋር ሰላም መሆን ይጠበቅብናል። የሰው ልጅ እንስሳዊ የሆነ ጊዜአዊ ስሜት፣ የሚያስተውል አእምሮ እና ሐሳብንና ድርጊትን ሁሉ መልካም ነው ወይስ ክፉ እያለ የሚያመዛዝን ኅሊና ያለው ፍጥረት ነው። ስለሆነምከራሳችን ጋር ሰላም መሆን ስንል ለኅሊና ወቀሳ የሚጋብዘንን፣ አእምሯችንን የሚረብሸንን ሥራ ከመሥራት መቆጥብ ይጠበቅብናል። ተሳስተን ብንሠራ እንኳ በንስሓ መመለስ ይኖርብናል። ከራስ ጋር ሰላም መሆን እያልን ያለነውም ይህንን ነው። ሁለተኛው ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም መሆን የሚለው ሲሆን ይኸውም ለሕግጋተ እግዚአብሔር መገዛትን የሚመለከት ነው። የእግዚአብሔር ቃል "ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ" ነውና የሚለው ትእዛዛቱን ጠብቀን ከእርሱ ጋር በፍቅር ከኖርን ሰላም ይኖረናል። ሦስተኛውና ካነሣነው ርእሰ ጉዳይ ጋር በቀጥታ የሚገናኘውደግሞ ከሰው ሁሉ ጋር ሰላም መሆን የሚለው ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም "ቢቻላችሁስ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ … ክፉን በመልካም ሥራ ድል ንሣው እንጂ ክፉን በክፉ ድል አትንሣው" በማለት ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም እንድንኖር መክሮናል። (ሮሜ፲፪፥፲፰-፳፩) እዚህ ላይ ከሰው ሁሉ የሚለው፣ ዘር ቀለም፣ የኑሮ ደረጃና አስተሳሰብ፣ እምነትና አመለካከት ወዘተ መሥፈርት አድርገን ሳንገድብ ከሁሉ ጋር መስማማት እንደሚገባን ያስገነዝበናል። ይህን ስንል ከመንፈሳዊ ግባችን ጋር የማይስማማ አመለካከትና አኗኗር ያላቸውን ሰዎች በክፉ ሥራቸው መተባበር አለብን ለማለት አይደለም። ከቻልን ወደ እውነተኛው የሕይወት መንገድ እንዲመጡ በምክር፣ በጸሎት እና በመልካም ምሳሌነት ማገዝ፤ ይህንማድረግ ባንችል እንኳ ለጠብ ከሚያነሣሡ ነገሮች ተቆጥበን በመከባበርና በመቻቻል ላይ በተመሠረተ ሕይወት መኖር ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የሰላምን አስፈላጊነት ሲናገር "ከሁሉ ጋር ወደ ሰላም ሩጡ፤ ቅድስናችሁንም አትተዉ፤ ያለ እርሱ ግን እግዚአብሔርን የሚያየው የለም" ብሏል። (ዕብ.፲፪፥፲፬) በሌላኛው መልእክቱ ደግሞ "የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ እንጂ መብልና መጠጥ አይደለምና" በማለት መንግሥተ እግዚአብሔር በራሱ ሰላም መሆኑን ያስረዳል። (ሮሜ፲፬፥፲፯)

**የሰላም ምንጭ እግዚአብሔር ሲሆን የሰው ልጅ ለሰላም ማጣቱ ምክንያት ደግሞ ዲያብሎስን በግብር መወዳጀት ነው።**

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ ወደ ሰማይ /ወደ ቀደመው ክብሩ/ እንደሚመለስ በነገራቸው ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ለማን ጥለኸን ትሔዳለህ ብለው መከፋታቸውን ተመልክቶ "ሰላምን እተውላችኋለሁሰላሜንም እሰጣችኋለሁ" በማለት አጽናንቷቸዋል። ይህንም ሲል እኔ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ አልለያችሁም ማለቱ ነው። ከዚህም በኋላ ሰላሙ ፍጹም መሆኑን ሲናገር "እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጠው አይደለም" ብሏል። (ዮሐ.፲፬፥፳፯)

ታዲያ ከሌሎች ጋር በሰላም ለመኖር ይህን ፍጹም ሰላም ለሌሎች ከማካፈል የበለጠ ምን መልካምነት ይገኛል? ዛሬ ዓለም ሰላም ነድሎታል። ወጥተው መግባት፣ ሠርተው መብላትና ሌሎችንም ሰላማዊ እንቅስቃሴዎችን ማከናወን ያቃታቸው በርካቶች ናቸው። ሰላም ከሰው ልጆች ከመራቁ የተነሣ ቤት ያፈራውን አብስለው መመገብ ባለመቻላቸው የሚራቡ ጥቂቶች አይደሉም። ለብዙ ሰው የሚበቃ ሀብትና ንብረት እያላቸው አንዱ አንዱን ለማጥፋት የሚያደቡ የቃየል የግብር ልጆችም በዝተዋል። ለእነዚህ ሁሉ የሰላሙን ምንጭ ክርስቶስን ልንሰብክላቸው የሰላም ሕይወት የሆናቸውን ክርስትናን ልናካፍላቸው ይገባል።

## መ. ፍቅርን ማካፈል፡-

ፍቅር የመንፈስ ፍሬ የሃይማኖት መሠረትእና የንጹሕ ልብ ምልክት ነው። ፍቅር የበጎ ሥራ ምክንያት የመተሳሰብና የደግነት ምንጭ በመሆኑ የመንፈሳዊ ሰው ዋናውና አቻ የማይገኝለት መገለጫው ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ፍቅር የመንፈሳዊነት መገለጫዎችን ሁሉ አጣምሮ መያዝ እንደሚችል ሲናገር "ፍቅር ያስታግሣል፤ ፍቅር ያስተዛዝናል፤ ፍቅር አያቅናናም፤ ፍቅር አያስመካም፤ ፍቅር አያስታብይም። ብቻዬን ይድላኝ አያሰኝም፤ አያበሳጭም፤ ክፉ ነገርን አያሳስብም። ጽድቅን በመሥራት ደስ ያሰኛል እንጂ ግፍ በመሥራት ደስ አያሰኝም በሁሉ ያቻችላል፤ በሁሉም ያስተማምናል፤ በሁሉም ተስፋ ያስደርጋል፣ በሁሉም ያስታግሣል" በማለት ፍቅር የመልካም ምግባራት ሁሉ ራስ መሆኑን ገልጾታል። (፩ኛቆሮ.፲፫፥፬-፯)

የሰው ልጆችን በዋናነት የሚያጣሏቸው እንደ ውሻም እርስ በእርስ የሚያናክሷቸው ጥቅም ቀረብኝ፣ ተበደልኩ፣ ክብሬ ተነካ፣ ተዋረድኩ ወዘተ የሚሉ የሥጋዊ ጥቅምና ክብር ጉዳዮች ናቸው። በዚህ በሐዋርያው መልእክት ላይ ደግሞ ፍቅር "ብቻዬን ይድላኝ አያሰኝም፤ ክፉ ነገርን አያሳስብም" የሚሉ ቃላት ይገኙበታል። እነዚህ የእውነተኛው ፍቅር መገለጫዎች ናቸው። የራሱ መሆኑን እያወቀ አሳልፎ ለሌላ የሚሰጥ እና በደልን የማይቆጥር፣ ለክብሩም የማይጨነቅ ሰው በምንም ምክንያት ከሰው አይጣላም። ቅዱሳን አባቶች ይህን በተግባር ፈጽመውታል። ለምሳሌ፡-

የአባ መቃርዮስን ታሪክ ስናነብ እንደምንረዳው ታላቁ አባት አባ መቃርዮስ ከዕለታት በአንድ ቀን ከበአቱ ውጭ ተቀምጦ ሳለ ሌባ ወደ በአቱ ገብቶ ያለውን ዕቃ ሁሉ ጭኖ ሊወጣ ሲል ደርሶበት የቀረውንም ዕቃ በመጫን ተባብሮታል። በስተመጨረሻ ላይ ግን ዕቃዎቹ የተጫኑበት ግመል አልነ ሣሲለው የቀረው ዕቃ ቢኖር ይሆናል በማለት ወደ በአቱ ገብቶ የቀረውን መኮትኮቻ አምጥቶ ሰጠው" ተብሎ ተጽፏል። (ዲያቆን ዳንኤል ክብረት፣ በበረሃው ጉያ ውስጥ፣ ፲፱፻፺፰ ዓ.ም ገጽ ፹፪) ይህም የሚያመለክተው በቅዱሳን ሕይወት ዘንድ የራስ የሆነውንም አለመፈለግን ነው። ሰማዕቱ ቅዱስ እስጢፋኖስም አይሁድ በድንጋይ እየወገሩት ሳለ "የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" ሲል ጸልዮላቸዋል (ሐዋ.፯፥፷)። ይህም በደልን አለመቁጠርን የሚገልጽ ነው። ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ "የእግዚአብሔርን

ቃል የተናገሩአችሁን መምህሮቻችሁን አስቡ መልካም ጠባያቸውን አይታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው" ብሎ የተናገረው:: (ዕብ.፲፫፥፯)

ዛሬ በዓለማችን ብዙ በፍቅር ስም የሚጠሩ ነገር ግን እውነተኛውን ፍቅር የማይወክሉ ነገሮች አሉ:: እውነተኛ ፍቅር ግን ክርስቶስ ዓለምን የወደደበት ፍቅር ብቻ ነው:: የክርስቶስ ፍቅር በዝምድና፣ በውለታና በስጦታ ላይም ያልተመሠረተ ንጹሕ ፍቅር ነው:: ቅዱስ ዮሐንስ ይህን ሲናገር ነው "ዓለምን እንዲሁ ወድዶታልና" ያለው:: (ዮሐ.፫፥፲፮) ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ "እኛ የእግዚአብሔር ጠላቶቹ ስንሆን በልጁ ሞት ይቅር ካለን ከታረቀን በኋላም በልጁ ሕይወት እንዴት የበለጠ ያድነን" ብሏል:: (ሮሜ፭፥፲) ዛሬ ዓለማችን ላይ ያለው ፍቅር ግን በደም /በዝምድና/ እና በውለታ በአጠቃላይ በጊዜያዊ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ነው:: ይህ ዓይነት ፍቅር የቃልና የአንደበት እንጂ እውነተኛ ስላልሆነ የመንፈሳዊነት መገለጫ ሊሆን አይችልም::

ፍቅር በሁለት ይመደባል:: ይኸውም ፍቅረ እግዚአብሔርና ፍቅረ ቢጽ (ሰውን መውደድ) ናቸው:: እግዚአብሔርን የሚወድ ትእዛዛቱን ይጠብቃል ሰውን የሚወድ ደግሞ መልካምን ሁሉ ያደርግለታል:: ማለትም ሰው ሰውን ከወደደ ሀብቱንና ገንዘቡን የእኔ ቢሆን ብሎ አይመኝም፤ በሐሰት አይመሰክርበትም፤ ገንዘቡንም አይሰርቅበትም፤ ይልቁንም ቢራብ ያበላዋል፤ ቢጠማ ያጠጣዋል፤ ቢታረዝ ያለብሰዋል፤ ቢታመም ይጠይቀዋል ቢታሰርም ያስፈታዋል እንጂ:: በዚህም ሕግን ሁሉ ይፈጽማል:: ሰውን የማይወድ ግን እግዚአብሔርን እወደዋለሁ ቢል ዋሽቷል:: "እግዚአብሔርን እወዳለሁ የሚል ወንድሙን ግን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው፤ የሚያየውን ወንድሙን የማይወድ ግን የማያየውን እግዚአብሔርን እንደምን ሊወድደው ይችላል?" እንዲል:: (፩ኛዮሐ.፬፥፳)

ስለዚህም በፍቅረ እግዚአብሔርና በፍቅረ ቢጽት እዛዛተ እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ ይፈጸማሉ:: "እርስ በርሳችሁ ከመዋደድ በቀር ለማንም ዕዳ አይሁንባችሁ ሌላውን የሚወድ ሕግን ፈጽሞታልና:: አታመንዝር፣ አትግደል፣ አትስረቅ፣ በውሸት አትመስክር፣ አትመኝ የሚለው ከሌላይቱ ትእዛዝ ሁሉ ጋር በዚህ ባልንጀራህን እንደነፍስህ ውደድ በሚለው ቃል ተጠቅልሎአል:: ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም ስለዚህ ፍቅር የሕግ ሁሉ ፍጻሜ ነው" እንዲል:: (ሮሜ፲፫፥፰-፲)

## መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ

በአጠቃላይ "መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ" በማለት ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ እንዳስተማረን እኛ በሐዋርያው ትምህርት ጸንተን መልካም ነገሮች ናቸው ብለን ከላይ የዘረዘርናቸውን ሃይማኖትን፣ በጎ ምግባርን፣ ሰላምንና ፍቅርን በውስጣችን አጽንተን መያዝ ይኖርብናል:: እነዚህን ነገሮች ለእኛ ብቻ እንድንኖራቸው ሳይሆን ለሌሎችም እንድናካፍል ተነግሮናል:: ደግሞ"ያለው ለሌለው ይስጥ" የሚለው የቅዱስ ወንጌል ትምህርት ሥጋዊ ፍላጎትን የሚያሟሉትን ነገሮች ብቻ ሳይሆን ዘለዓለማዊ ርስትን የሚያወርሱትን ሁሉ ነውና እነዚህን በጎነቶች ለእኛ አጽንተን መያዝ ለሌላውም ማካፈል ይኖርብናል:: ለዚህ ሁሉ ደግሞ እግዚአብሔር ሲፈቅድ ነውና ሃይማኖትን፣ በጎ ምግባርን፣ ሰላምንና ፍቅርን እኛ ኑረንባቸው ለሌላውም አካፍለን የመንግሥቱ ወራሾች የስሙ ቀዳሾች እንድንሆን የእግዚአብሔር ቸርነት፣ የድንግል ማርያም አማላጅነት፣ የቅዱሳን ሁሉ ተራዳኢነት አይለየን አሜን::

# ባለህበት ጽና

## ኪነ ጥበብ

*በእንዳለ ደምስ*

በደቡብ ኦሞ የቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን ቀዳሽ ካህን የሆኑት ቀሲስ ተውህቦ ይሔይስ ኪዳን አድርሰው ምእመናንን ካሰናበቱ በኋላ ልብሰ ተክህኖአቸውን እንደለበሱ ቤተልሔም መግቢያ በር ላይ ካለው አግዳሚ ወንበር ተክዘው ቁጭ ብለዋል። ጠይም፣ ቀጭን፣ በግምት በአርባዎቹ የዕድሜ ክልል ላይ የሚገኙ አባት ናቸው።

በአባታቸው አባ ይሔይስ ዘመን የቤተ ክርስቲያኑ አገልጋዮች ቁጥር ስፍር አልነበራቸውም። ከፊሎቹ ከዚህ ቤተ መቅደስ አልፈው ለሌሎች አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ይተርፉ እንደነበር ያስታውሳሉ። ቤተ ክርስቲያኑ ሲመሠረት ጀምሮ የመጀመሪያው አገልጋይ ቀሲስ ይሔይስ ሲሆኑ ከሰማንያ ዓመታት በላይ አገልግለው ዕድሜ ገድቧቸው ካረፉ ዐሥር ዓመት አልፎታል።

ከልጆቻቸው የአባታቸውን ፈለግ የተከተሉት ቀሲስ ተውህቦ ብቻ ሲሆኑ ከሕፃንነት ጀምሮ በአባታቸው እግር ሥር ሆነው ከፊደል እስከ ፲፬ቱ ቅዳሴያት ተምረዋል፤ ቤተ ክርስቲያኑንም የማስተዳደር ኃላፊነት አባታቸው ካረፉ በኋላ ተረክበው አቅማቸው የፈቀደውን ሁሉ አገልግሎት በመፈጸም ላይ ይገኛሉ። ነገር ግን ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ አገልጋይ ካህናትና ዲያቆናት ቤተ ክስቲያኑን ጥለው እየወጡ የተሻለ ክፍያ ወዳለበት ወደ ከተማ በመኮብለላቸው ተጨንቀዋል። የቀሩት እሳቸውና ሁለቱ ዲያቆናት ልጆቻቸው ብቻ በመሆናቸው ለምእመናን ቅዳሴ ቀደሰው ለማቁረብ፣ ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው የምታከናውናቸውን ሃይማኖታዊ አገልግሎት ለመፈጸም ተቸግረዋል።

በቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ውስጥ ጸጥታ ሰፍኗል፣ ቤተ ክርስቲያኑን ከበው የሚገኙት ሀገር በቀል ዛፎች ቅርንጫፎቻቸው ብቻ የነፋሱን እንቅስቃሴ ተከትለው ይወዛወዛሉ፣ ቀሲስ ተውህቦም እንደ ዛፎቹ ቅርንጫፎች በሐሳብ አንዱን እየጣሉ አንዱን እያነሱ ከራሳቸው ጋር ሙግት ገጥመዋል።

-"እኔም ጥዬ ልሂድ ይሆን? ዲያቆናቱም ሆነ ካህናቱ የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ከተማ ናፍቀው ሔደዋል፤ እኔ ብቻዬን እዚህ ምን እሠራለሁ? የአባቴን የአደራ ቃልስ ምን ላድርገው? ቤተሰቤስ፣ እጠብቃቸው ዘንድ ከእግዚአብሔር የተሰጡኝ ምእመናን በጎቼን ለማን በትኜ እሔዳለሁ፣ ለተኩላ አሳልፌ ሰጠኋቸው ማለት አይደል? እግዚአብሔር እንደነፈቀደው ያድረገኝ እንጂ ሌላው አደረገው ብዬስ እኔ አላደርገውም" አሉ ለራሳቸው የእጅ መስቀላቸውን በትካዜ እያገላበጡ።

ከአንድ ወር በፊት አብሮ አደግ ወዳጃቸውና የዚሁ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የሆኑት ቀሲስ ጥላሁን ከኪዳን ጸሎት በኋላ ከቤተ መቅደስ እየወጡ "አንድ መረጃ ይኸለሁ። ብንነጋገርበት ጥሩ ነው" በማለት ቀሲስ ተውህቦን እንደሚፈልጓቸው ይነግሯቸዋል።

"በሰላም ነው የፈለግኸኝ?" አሉ ቀሲስ ተውህቦ ከቤተ መቅደስ እየወጡ።

"አዎ። ካሰብንበት መታደል ነው" አሉ ግቢው ውስጥ ዛፍ ሥር ካለው መቀመጫ አረፍ እያሉ።

"በል ንገረኝ ልስማዋ" አሉ ቀሲስ ተውህቦ ለመስማት ጓጉተው ቀሲስ ጥላሁን አጠገብ እየተቀመጡ።

"ዕድሉን ከተጠቀምንበት ሕይወታችን ይቀየራል:: መልካም ዜና ደርሶኛል፤ እንደምንም ተቸግረንም ቢሆን ሌሎች ወንድሞቻችን የደረሱበት መድረስ አለብን:: እኛ የተሻለ ኑሮ አያምርበብንም እንዴ?" አሉ::

"ለምን አትነግረኝም?"

"ምን መሰለህ፤ ስንት ዓመት እዚህ ገጠር ውስጥ እንዳገለገልን ታውቃለህ? ይኸው አርባ ዓመታ አለፈን:: የተለወጥነው ነገር አለ? ትላንትም ድሃ ነበርን ዛሬም ድሃ ነን፣ ከድህነት ሌላ ምን አተረፍን?" አሉ ቀሲስ ጥላሁን ትላንትን እየረገሙ::

"አልገባኝም:: ለምን ዳር ዳር ትላለህ ተናገረው እንጂ" አሉ ቀሲስ ተውህቦ ለመስማት የነበራቸው ፍላጎት ከስሞ በንዴት እየተመለከቷቸው::

"እዚህ አብረውን ሲያገለግሉ የነበሩ ካህናት ምን ያህል እንደነበሩ የሚያውቁት ጉዳይ ነው:: አንድ አንድ እያሉ ድህነትን ለማምለጥ ወደ ከተማ ገቡ:: ሁሉም ተሳክቶላቸዋል፣ የደብር አለቃም የሆኑ አሉ፣ በየወሩ ከሦስት ሺህ ብር በላይ የሚከፈላቸውም አሉ:: እኛ እዚህ ተቀምጠን ድህነት ውጦናል፣ መቼ ነው ደህና ልብስ የምንለብሰው? መቼ ነው ልጆቻችንን ደህና ትምህርት ቤት የምናስተምረው? እዚሁ ተወልደን እዚሁ ልንሞት ነው?" አሉ ቀሲስ ጥላሁን ቀሲስ ተውህቦን ለማሳመንና ልባቸውን ለማሸፈት እየሞከሩ::

"እና ምን እናድርግ ነው የሚሉኝ?" ሁለቱም አንቱ የሚል የመከባበር ቅጽል ይጠቀማሉ::

"አንድ ታማኝ ሰው አግኝቻለሁ::"

"ምን የሚያደርግ?"

"ከተማ ላይ ካሉ አብያተ ክርስቲያናት የሚያስቀጥር::"

"እኔ ቀዬን ትቼ የትም አልሔድም:: እትብቴ የተቀበረበት፣ ክርስትና የተነሳሁበት፣ ከልጅነት እስከ ዕውቀት ያገለገልኩበትን ቤተ መቅደስ ዘግቼ፣ ግራ ቀኛቸውን የማያውቁ በጎቼን በትኜ፣ ለአውሬ ሰጥቼ የትም አልሔድም" አሉ ቀሲስ ተውህቦ በንዴት::

"ትንሽ ብር ነው የምንጠየቀው፣ መክፈል ያቅተናል ብለው ፈርተው እንዳይሆን::"

"እርስዎ መሄድ ይችላሉ፣ እኔ አደራዬን ትቼ ከዚህ የትም አልንቀሳቀስም::"

"ስንት ብር መሰሎት የጠየቀው ለእያንዳንዳችን ሃያ ሺህ ብር ብቻ ነው:: ካስታወሱ እነ ቀሲስ ትእዛዙ የዛሬ ሁለት ዓመት ከዚህ ሲሔዱ የከፈሉት ሠላሳ ሺህ ነበር:: ለእኛ ብዙ ቅናሽ ነው ያደረገልን" አሉ ቀሲስ ጥላሁን የወዳጃቸውን መበሳጨት ወደ ጎን በመተው::

"መሄድ ይችላሉ:: እኔ ሳይገባኝ ሥልጣነ ክህነትን የተቀበልኩት አምላኬ የደረሰበትን መከራ መስቀል እንዳስብ፣ በታማኝነት እስከ ሞት ድረስ እንዳገለግል እንጂ ለድሎት አይደለም:: ይቅርታ አድርጉልኝ በሐሳብዎ አልስማማም::"

"በሉ እንግዲህ ከነድህነትዎ ይኑሩ" ብለው ቀሲስ ጥላሁን ተስፋ ቆርጠው ትተዋቸው ከቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ወጡ::

አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አዲስ አበባ መጥተው የመቀጠራቸውን ዜና ምሽቱን ነበር ሰሙት::

✞ ✞ ✞

ቀሲስ ተውህቦ ከቤተልሔሙ አጥር ጥግ ካለው አግዳሚ ወንበር ላይ እንደተቀመጡ ልቡናቸው በሁለት ጥጋቸውን በያዙና ሊቀራረቡ እንኳን በማይችሉ ተቃራኒ ሐሳቦች ተከፍሎ ቆየ፡፡

-"እዚህ ምን ታደርጋለህ? ዘመኑ ተቀይሯል፣ ትንሽ ብር ከፍለህ ብዙ ወደሚገኝበት ከተማ ኮብልል፣ በአንድ ዓመት ተለውጠህ ትመጣለህ፡፡ አደራ አለብኝ እያልክ ወደ ኋላ አትቅር፡፡ ሒድ ሒድ…" ይላቸዋል አንደኛው ጽንፍ ሐሳብ፡፡

-"ይህ የሕይወትህ መሠረት የተጣለበት ቦታ ነው፡፡ እግዚአብሔርን ታገለግል ዘንድ የተሾምክበት ሥፍራ ስለሆነ የገባኸውን ቃል አትጠፍ፤ አባትህ እግዚአብሔር ፈቅዶላቸው ያጸኑት ቦታ ነው፡፡ እግዚአብሔር የሰጠህን መንጋ የት በትነህ ትሔዳለህ? ቆም ብለህ አስብ፣ መንገድህን አትሳት፣ እንደ ኤሳው በረከትህን አታስወስድ፣ ይህንን አገልግሎት ወደ ልጆችህ ለማስተላለፍ ያደረግኸውን ትጋት አስብ፣ ዛሬ ልጆችህ ደርሰውልሃል፣ ለዲቁና አብቅተሃል፣ አባትህ አንተን በመንገዱ እንደመራህ ልጆችህንም ምራቸው፡፡ አገልግሎትህን የሚረከቡ የአብራክህ ክፋይ ያገኘኸው በዚህ ቤተ መቅደስ አገልግሎትህ ነው፣ ይህ ሥፍራ ባለውለታህ እንደሆነ አስብ፣ ለአንተ የተፈቀደ ቦታ ይህ ነው፣ የትም አትሒድ ባለህበት ጽና …" ይላቸዋል፡፡ ተጨነቁ፡፡

ቀስ በቀስ ግን ሂድ- ሂድ እያለ ሲገፋቸው የነበረው ስሜት እየበረደ እዚሁ ቤተ ክርስቲያንን እያገለገሉ ከሚወዱትና ከሚወዳቸው ሕዝባቸው ጋር ለመኖር፣ ልጆቻቸውንና ሌሎችን ለማስተማር፣ ተተኪ ለማፍራት ቃል ገቡ፡፡

## ከመጽሐፍ ቅዱስ ምክሮች

- ✞ ለሚያደርጋት ሁሉ ምክር መልካም ናት፤ ምስጋናውም ለዘለዓለም ይኖራል፡፡ *(መዝ.፻፲፥፲)*
- ✞ ለባልንጀራው ጉድጓድን የሚምስ ይወድቅበታል፣ ቅጥርን የሚያፈርስም እባብ ትነድፈዋለች *(መክ.፲፥፰)*
- ✞ ሕፃንነትና ጉብዝና አለማወቅም ከንቱ ናቸውና ከልብህ ቍጣን አርቅ፤ ከሰውነትህም ክፉ ነገርን አስወግድ *(መክ.፲፩፥፲)*
- ✞ እግዚአብሔርን አንዲት ነገር ለመንሁት እርስዋንም እሻለሁ፤ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት እኖር ዘንድ፣ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውንም አይ ዘንድ፣ በቤተ መቅደሱም አገለግል ዘንድ፡፡ *(መዝ.፳፮፥፬)*

# ቅጽል



በዲ/ን ዐቢይ ሙሉቀን

ቅጽል፡- ከቃል ክፍሎች አንዱ ሲሆን የሚጨመር፣ የሚቀጠል ማለት ነው። መምህር ዕንባቆም የግእዝ ቋንቋ የሰዋስው መጽሐፍ ለተማሪዎች በልዩ አቀራረብ የተዘጋጀ በተሰኘ መጽሐፋቸው “ቅጽል ማለት ተቀጸለ ተቀዳጀ ከሚለው ግስ የተገኘ የባለቤትን ጠባይና ግብር፣ መልክና ዓይነት፣ መጠንና አኳኋን፣ ወርድና ቁመት፣ስፍርና ቁጥርን የሚገልጽ ሲሆን ከስም በፊትና በኋላ በመግባት ይቀጸላል” በማለት ያስረዳሉ። ከመምህር ዕንባቆም አገላለጽ እንደምንረዳው ቅጽል ተጨማሪ፣ ቅጥያ፣ ስምን ተከትሎ ወይም ቀድሞ የሚገባ እና ስምን ከልዩ ልዩ ጉዳዮች አንጻር የሚገልጽ ማለት ነው። ከልዩ ልዩ ጉዳዮች አንጻር ማለትም ከመጠን፣ ከዓይነት፣ ከግብር፣ ከጸባይ ወዘተ አንጻር ስምን ለመግለጽ የሚያገለግል ማለት ነው።

አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌም መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ በተሰኘ መጽሐፋቸው “ቀጸላ፤ ቅጽል በስምና በግብር የሚጨመር ቃል የአካልንና የግብርን አኳኋን ጠባዩን፣ መልኩን የሚገልጥና የሚያስረዳ ። ነዊኅ፣ ሠናይ፣ ጸዐዳ” እንደማለት ነው። (ኪዳነ ወልድ፣ ገጽ ፹፻፬) በማለት ያስረዳሉ። የአለቃ ኪዳነ ወልድን አገላለጽም ስንመለከት ከላይኛው ጋር ተቀራራቢ በሆነ መልኩ እንደተገለጸ እንረዳለን።

ዓለማየሁ ሞገስ ሰዋስወ ግእዝ በተባለ መጽሐፋቸው “የአንድን ነገር ዓይነትና መጠን፣ አቅምንና ግብርን የምንለይበት ቃል ቅጽል ይባላል። ቀይህ፣ ጸሊም፣ ኀጺር፣ ኃያል፣ ነዊኅ፣ ዐቢይ፣ ግዙፍ፣ እኩይ፣ ሀካይ …አሁን የጠቀስናቸው ቃላት ሁሉ ከስም ተጠግተው ምንነቱንና ዓይነቱን ስለሚነግሩ ቅጽል ይባላሉ” ሰዋስወ ግእዝ፣ገጽ፲፬) በማለት የቅጽልን ምንነትና አገልግሎት እንዲሁም የስያሜውንም መሠረት ያስረዳሉ። ከጥቅሱ እንደምንረዳው ቅጽል ከስም ጋር ተጠግቶ ስምን የሚገልጽ ነው። ቅጽል ዋና ተግባሩ ስምን መግለጽ ስለሆነ አንዳንዴ የስም ገላጭ እየተባለም ይጠራል።

ቅጽል በግእዝ ቋንቋም ሆነ በሌሎች ቋንቋዎች ስም ላይ ተጨምሮ ስምን ከመጠን፣ ከዓይነት፣ ከግብር፣ ወዘተ አንጻር የሚገልጽ የቃል ክፍል እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ልዩነት ሊኖር የሚችለው የቅጽል ዓይነቶች ላይ ነው። ለምሳሌ በአንድ ቋንቋ ቅጽል የተባለው በሌላው ቋንቋ መስተአምር ሊባል ይችላል። ይህ ደግሞ የቃል ክፍሎች አመዳደብ ላይ የሚፈጠር ልዩነት ነው። ይህን ጉዳይ በምሳሌ ለማስረዳት በግእዝ ቋንቋ አኃዝ ቅጽል የሚባሉት አሐዱ፣ ክልኤቱ፣ ሠለስቱ፣ አርባዕቱ… በአማርኛ ቋንቋ ግን መስተአምር ተብለው ይመደባሉ። እንደ አጠቃላይ ለቅጽል በሚሰጡት ብያኔና ተግባር ግን ተመሳሳይነት እንዳለው ለመረዳት በየቋንቋዎች የሚሰጠውን ብያኔና ተግባር መመልከቱ በቂ ነው።

የበለጠ ግልጽ ለማድረግ ቅጽል ስም ላይ ተጨምሮ ስምን ከመጠን፣ ከዓይነት፣ ከግብር፣ ከመልክ ወዘተ አንጻር ይገልጻል ብለናልና በዚህ መልኩ በምሳሌ እንመልከተው።

መጠንን ሲገልጽ፡- ንኡስ አነ እምአኃውየ ወወሬዛ በቤተ አቡየ፤ ከወንድሞቼ ሁሉ ታናሽ ነኝ በአባቴ ቤትም ታዳጊ ነኝ። (መዝ.፻፶፩ በእንተ ርእሱ)

ግብርን ሲገልጽ፡- ቀዳሲ ካህን ይትከበር በኀበ ኵሉ ሕዝብ፤ ቀዳሽ ካህን በሕዝቡ ሁሉ ዘንድ ይከበራል።

መልክን ሲገልጽ፡- እንዘ ተሐቅፊዮ ለሕፃንኪ ጽጌ ጸዐዳ ወቀይሕ፤ ነጭና ቀይ አበባ የተባለ ልጅሽን ታቅፊሽ (ማሕሌተ ጽጌ)

ጸባይን ሲገልጽ፡- "ኵኑ እንከ የዋሃነ ከመ ርግብ ወጠቢባነ ከመ አርዌ ምድር፤ እንደ ርግብ የዋሆች እንደ እባብ ልባሞች ሁኑ። (ማቴ.፲፥፲፮)

ልበ ትሑተ ወየዋሃ ኢይሜንን እግዚአብሔር፤ የተዋረደውንና የዋሁን ልብ እግዚአብሔር አይንቅም። (መዝ.፶፥፲፯)

ወገንንና ግብርን ሲገልጽ፡- ኤፍሬም ሶርያዊ ኤፍሬም ለብሓዊ፤ የሶርያ ሰው የሆነ ኤፍሬም፣ ለብሓዊ ኤፍሬም (ሶርያዊ በሀገሩ ለብሐዊ በተግባሩ)

ሶርያዊ የሚለው ወገን አመልካች ሲሆን ለብሓዊ የሚለው ደግሞ ግብር አመልካች ነው። ቅዱስ ኤፍሬም የከበሩ ዕቃዎችን እንደብርሌ፣ ብርጭቆ የመሳሰሉትን የእጅ ሥራ እየሠራ ይኖር ስለነበር ለብሓዊ ተብሏል። በሀገሩ ደግሞ ሶርያዊ ተብሏል።

ቁጥርን ሲገልጽ፡- ወሀሎ አሐዱ ብእሲ እምፈሪሳውያን ዘስሙ ኒቆዲሞስ መልአኮሙ ለአይሁድ ፤ከፈሪሳውያን ወገን ኒቆዲሞስ የተባለ የአይሁድ አለቃ አንድ ሰው ነበረ። (ዮሐ.፫፥፩)

ወናሁ መጽአ አሐዱ ብእሲ ዘለምጽ ወቀርበ ኀቤሁ ወሰገደ ሎቱ፤ አንድ ለምጻም ሰው መጣና ወደ እርሱ ቀርቦ ሰገደለት። (ማቴ.፰፥፪)

ውድ አንባብያን በሚቀጥሉት እትሞቻችን የቅጽል ዓይነቶችንና የእያንዳንዱን ተግባር በሰፊው የምንመለከት ይሆናል።

## ሥራህን ሥራ

በሁዳዱ መሬት መልካም በሚያፈራው
ሠራተኛው ጥቂት መኸሩ ብዙ ነው
　　የእርሻው ጦሙን ማደር አንተን አስጨንቆህ
　　ከወጣህ ልትሠራ ወገብህን ታጥቀህ
አንተ ! ብርቱ ኀበዝ እጅግ ደስ ይበልህ
የደረቀ መሬት . . . አለስልሰህ ዘርተህ
የአበባው ግዜ አልፎ . . . ፍሬውን ታያለህ
　　በሥራህ በርትተህ . . . ፀሐይ ብትጠልቅም ምሽቱም ቢነጋ
　　ሰነፍ ቢያንጓጥጥህ በነገር ቢተጋ
መልስ ለመመለስ . . . ወደ ኋላ አትዙር . . . በከንቱ አትድከም
ማሳው እንዳይጠፋ . . . እንዳይበላው አረም
　　የተዘራው ፍሬ ሠላሳ እና ስልሳ መቶም እንዲያፈራ
　　የተሰጠኽውን . . . ሥራ ብቻ ሥራ።
　　የተሰጠኽውን . . . ሥራ ብቻ ሥራ።

*ከመዝሙርና ኪነ ጥበባት ማስተባበሪያ*